Image



© መብቱ በሕጉ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

የመጀመሪያ ዕትም ዘኒ 2007
First Published June 2015
Addis Ababa, Ethiopia

ለአስተያየትዎ
Email: mirumercy@gmail.com
Facebook: LelaSew ሌላው በምህረት

ለሚታገኙ ...

ላረፈዱ ... ለተሰወረ
መጣሁ እያለ ... ብዙ ለቀየ

ይሁን ...

oin here

እንዳትነኩት

ክፍል ፩

የመዳረሻው መነሻ

፡ 1 ፡

ግራሚ ... ነው የሚጠቀርበትና ጥቀርም የሚነግበበት ስፈራ ገባት ነው። የሕይወት መልኳ አሰር እጅ የቀርና ነው ... የቀረው ደግሞ ግራሚ ነው ሊባል ይችላል። ግራሚ የብርሃን ከረሪያ ወይም የጨለማ ፈገግታ ሆና ይታያል ... ወደ አንደኛው ገዝ እየደደም ... የራሱም መልክ የለውም ... ብሉ መከራ-ዝርም ይቻላል። በሴላ በኩል ሁሉም ቀለማት ዘቦመልካቸው ሰፊ የግራሚ ይርዝ አላቸው። ሰው የመሆን ለላነትና የውነትም ... በራሱ ስፈ ግራሚነት ውስጥ ተሰውር ተገልጧል። እያንዳንዱ ሰው ሴላ ሰው ... ሴላውም ሰው ያው እንደ እሮው ሰው መሆኑን መረዳት አንዱ ግራሚ የእደወት አተያይ ነው።'

ጾሀቲር ልላሙው ከንባበት የግራሚ ያላብ ውስጥ የእሀቱ ሰልክ መንጭቶ አውጭ፣ እያመራ ማስጠና እያስበ ማውራት፣ ከሥራው የተማረው የዘወትር ልማዱ ሆኗል። ነገና ጥቁር እይታም እየጋረጸት የርሱን ግራሚ ዓለም መረዳት እንደ ተሳናት ስሚያስባት እሀቱ ጋር መነጋገርና መግባባት እየተሳነው መጥቷል።

'እቲቷ ... ምንም ብልሽ የኔ ያሳብ ሊገባሽም ሆነ ሊስማማሽ አይችልም' አለ፣ እጁን እያወናጨፈ ከበረንዳው ወጥቶ፣ ከሊኒኩ ዝቢ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያለ። የሰልኩ ምንድ ከዚርው ውስጥ እየተቀራረጠ ሰላለቻገረው ነው ወደ ሙጫ የወጣው።

ከታላት እሀቱ ጋር ቃዝቀዝ ብለው የጀመሩት የስልክ መረ ወደ ጋስ ንትርክ ተቀየረ። 'የማይገባኝ ከሆነ ታዲያ ለምን አታስረዳኝም?' ብላ፣ በደረቁ ስትስት የበለጠ ቀስጫ። ውልገጸም እንደ ልጅ የምታየው ይመስለዋል።

'እሺ ... አንድ ጊዜ በደንብ ስሚኝ። ለእኔ፣ ስኬትና ምቾት ስትኖረ የምታገኟቸው የሥራ ፍሬዎች ናቸው እንጂ የምትኖረላቸው የሕይወት ዋናና አላማዎች አይደሉም። የመኖር ትርጉምን ሊሰዋ የሚችል ኃይል በውስጣቸው የለም። እኔ ወደ ሀገር ቤት የተመለስኩት የሕይወቴን ዋሪ ለመፈጸምና እድሜ ልኬን ሊያስቃዩኝ ለሆኑ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ነው። ይህንን ደግሞ ለገዜህም ላስረዳት ብሎ ላይጨርስ አቋረጠችው።

'ስማ ልላ፣ በማዩ ሞት እኔ ያንተን የማያልቅ የናልስናና ዲስኩር መስማት ለልጥየሀል። ደግሞ ... እድሜ ልክህን ስትጓቃዩ ከሚፍ ምክንያት ማጣት በየቦከሙ ድምጽ። የአስራ አንደኛ ለላየ ፈገግ ሆና መደ አሜሪካ ለደይ ቃቀብላ ያስተናንደችውና ያስተማረችው እስ በዩል ፈገግ ሆና መደ አሜሪካ ለደይ ቃቀብላ ያስተናንደችውና ያስተማረችው እስ ናት። በመስከላቸው የአስር አምስት ዓመት ልዩነት በሙኖሩ እንደ ሁልተኛ እናቱ ነው የሚሰያት።

'እቪ የደ ምን አደርጉ ነው የምትዪኝ? አዚህ የጀመርኩትን ንገር ሁሉ በትጉ፣ ፍጥነፀ እንድጨነ ነው የምትፈልጊው? ብመጣስ ሰምን ነው? ከዚህ በኋላ ሁሉም ንገር የነፃቸዋል ስለዚህ መደ አዚህ የመጣኝን ተጻዩ ከሚፍ ዓላደርስ መመሰስ አልችልም። አ፡ ቀጮ ዓለ ድምጽ ሊ ግባው እንድማይችሉ ቢገባውም ተስፋ ሳይቀርጥ የንግግሩን አቅጣጫ ቀደር ሁኔታውን ሊያስረዳት ያደረገው ሙከራ ሊሳካለት አልቻለም።

'ስማ ልላ ... ሚስትህንና ልጆችህን ላንዲና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጣት ካልፈለግህ ደሃ ብዋኖ ልድልህ ነው። ቀደ አንተ ግን ... ምንድነው የንካህ ነገር? ቢያንስ ልጆቹ አያስጸሀም? እቢስ ብትሆን በዚህ አገር ኑሮ ሁለት ልጆች ይዛ ላይ ታች ስትግስን ምንደው ልብህን እንዲህ ያደነደነው?' አለች።

የልጆቹና የሚስቱ ነገር ሲነሣ ሰውነቱ ሲገል ተስግው። ውስጡ ግልቀስ በፈልግ ስሜቱን እንደምንም ተቀግስረው። ሰው በሴለበት ሚካ መሃል ወደም ያየራ ሚፍ ላይ ቀሞ እሪ ብሉ መጮህ አማረው። ላያስበው የውጪው በር ጋ ሲናርጌ፣ የዘቃው ልላልዘሩ በሩን ከፍቶ እግሩ ወጻመራው አትጣጫ ወጥቶ ሄደ። እሱ ስታወራ ጆሮው ቢሰማትም በሞንቅላቱ ውስጥ ባለው የሁሳብ ሚሚታ ተውጦ በቀኖኗ የመጠር መንገድ ቀልቁል መረደ። ስልኩ ድንገት ሲጥረጥ አየት አደረገውና ከእጁ ላይ አቨቀንኖር ሊወረውረው ፈለገ። እጆቹን እሱረው ኪስ ውስጥ ከትቶ በጀኖ ቀልቁለቁን መራመዱን ቀጠለ።

ከየናው አስፋልት ከመግባቱ በፊት ካለች አንዲት ሱቅ ገብቶ ፓኮ ሮዝማን ሲገራ ዘ፡ ከአስራ አምስት አመት በኋላ ሲጋራ በእጁ ሲንካ የመጀመሪያ ጊዜው ነው። ወዲያው ወደ ዋናው መንገድ እንደታጠፈ አንዲት ትንሽ ካፈ በረንዳ ላይ ተቀመጠ። ኪፖኩ ያወጣትን ሲጋራ አያፍተለተለ አመነታ። ሲጋራዋን እያነደደ በሚወጣው የሚትነበኔ ጭስ ውስጥ ታሩና ... የውስጥ ስቃዩን ሊደብቅ ፈለገ። ቡና እንደወረደ አዘና ደንግም በረጅሙ ተነፈሰ። መራራውን ጥቁር ቡና በትኩሱ ቆት ቆት ብሉ ወለው፣ ከብዙ ትግል በኋላ ያወጣትን ሲጋራ እያመነታ ወደ መጣችበት መለሳት። ሙሉ ያኩን ጨመደዶ ከባደው ስኒ ውስጥ ጨምሮ ጠቀጠቀው። ሒሳቡን ከስኒው ግስቀመጫ ስር አስቀመጠና ወደ ዋናው መንገድ ገብቶ እግሩን ተከትሎ ተጓዘ።

ጾለያግ ሆና የየለው የአዲስ አባባ ሰማይ ከወደ ሰሜን ምሥራቅ በመጣው የጭር ደመና ሊሸፈን ከተማይቱ ፈክቶ የሞለ ፊቷን ባንዴ አጨፈግገችው። ሰማዩን ያጨለመው ጾሩ ያረገዘው ደመና የተሸከመውን ውኃ ከተማይቱ ላይ ለመዘርገፍ አቀፋበ፣ ልብን በሚስጥቀው መብረቁ ነጭድጓዱ እያምባረቀ በማን አለብኝነት

ሙሴ ሙሴ ይላል፣ ባር ቅጠሉን እያንዣበ እየጣለ የሚያቆጨው ነፋስ ደንቅ የሙሾውን ክቦር ከሰማዩ ገጽ ላይ ሊያኮርር ይመስል በምታ ንጋረት ጎደንት ዋድሬን እመዲያ ወደሀ ሪራመሳል፣ የንያላት አለዋ እግ ያስጨነቃቸው ሕያዋን ፍጥረት ከመሰለየው ነፋተው ሊሸሸጉ ቢያቅጣጫው ይጣደፋሉ። የውሾች ጩኸትና የሰዎች ሩጫ ... የታስሬዎች ውሽልና የሳርች ፎ.ፎ.ታ ... የፈጠረው ድብልቅልቅ ትርምስ ብረሩ ብረሩ የሚያስኝልብ የሚያባባስሜትን ያሞራል።

የአቡ ቅጽታበና የሰማዩ ፍጥነቱን ጨምሮ ወደ ክሊኒኩ አቅጣጫ ተመለሰ። ዶክተሩ ያላሳው ሴላመው ፍጥነቱን ጨምሮ ወደ ክሊኒኩ አቅጣጫ ተመለሰ። ወደ ተዋና መንገድ ሲደርስ መንገሰከብ የጀመረው ዝናብ ባንድ ጊዜ መለተ ያቆመ ብረሄው። እኔሬ አውጪ ችሮ የውጪው ደጅ ጋ ሲደርስ በሩ ከውስጥ ተቀልፎ አሳ ነበር መክየት አልቻለም። ባለ በልዳ አቅጫ እያንኳኳ ከበሩ ስር ለመጠለል ሞከረ። የዚያው ለምታው እስኪከፍቱለት ድረስ ሁሉንተናው በውሃ ተጠመቀ። እስኪ ቢፋ ሊሸኙት ሆንየሳሉትም ቢያጠራጥራቸው "የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም" ኅይኑት ትታኖው ርጠ።

በረንዳው ላይ ደርሶ ከላይ እስከ ታች በልብሱ የተሸከመውን ውኃ ሲጨምቀው ትንሽ ጽናፍ ፈጠረ። ሰው ሁሉ በየቢሮው ተወሽቆ ሰለንበር ማንም አሳየውም። በነገ ባለው በር ወደ ራሱ ቢሮ እንደገባ በፍጥነት ልብሱን ቀየረ። ጠዋት ለሰፖርት መሄሪያ ከያዘው ቦርሳ ውስጥ ያለውን ልብስ ሲለውጥ አጥንቱ ውስጥ የገባው ብርድ ትንሽ ጋብ አለለት። ለእቀን ሲያይ ለአስራ አንድ ሰአት ሩብ ጉዳይ ይላል። ከውሃ ማጣሪያው ውስጥ የፈላ ውሃ ቀድቶ ሻይ ቅጠል ጨመረና ራሱን ለማምጮት ሞከረ።

ተወትሮዉት የማያውቀውን ከወደ ጥፕ ያለውን የእሳት ማንደጃ ቀረብ ብሉ አየው። ውስጡ የተረበረበው ፍልጥ እንጨት የአንዳጅ ያለህ ይመስል ደረቁን ገልጿል ተንድሟል። ወደ ካርድ ክፍል ደውሎ የጽዳት ሠራተኛዋን እንዲልኩለት ነገራቸው። በሩን እንኳኩታ አንገቷን ብቅ ሲታደርግ ሰላም ካላት በኋላ፣ "ደጅ ወዋቹ ዝናቡ መርዶብኝ፣ በብርድ መሞቷ ነው ባክሽ። እደህ ምድጃ ውስጥ ያለውን እንጨት እሳት ፊታያደጀልኝ ብዙ ነው፣ ክብሪትና ጋዝ ነገር ካለ በቂ ነው" አላት።

"ውይ በሞትኩት ... ብርዱ እኮ እንዲሁም እዋንት ይሰብራል። መጣሁ እሰኪ" ብላ፣ በሩን መልሳ ዘጋችው። ብዙም ሳትቀይ እሳቱን አያይዛለት ስትወጣ ሶፋውን ሳብ አድርጎ ወደ እሳቱ ተጠግቶ ተቀመጠ። የበለጠ እንዲነድ አየቀሰቀሰ ብርዱ ያቀረፈቀውን እደና እጁና ጠጋ አድርጎ ለማሞቅ ሞከረ።

ከተቀመጠበት ተነሥቶ ትንሽ ወዲያ ወዲህ ሲል ቀየ። ወደ ጓሮ ከሚያሳየው ሰፊ መስኮት አንዱር ሄዶ እጁን ጨበጥ ላላ እያደረገ ዋቂት ቀመ። አውን ዝናቡ ሙሉ ለሙሉ ቀኗል። በሞሃ ቅጠል ላይ የተከማቸው ውሃ ወደ መሬት ይንጠባጠባል። ለመዋለት የቂት የቀሪት ይምዝር የመጨረሻው ሙቀት አልባ ቀይ ብርቱካንማ ቀለሟን ገፈገፍታ በወረደው ደፍ ለተወገሩ ፍጠራን ሃጢታዋን የምትገልጽ ትመስላለች። ውሎዎ ነገር ረዋና ጸጥ ብሏል፣ ከሌላው ውሲጠ ነፍስ በቀር። ወደ ሥራ ጠረጲዛው ሃሪና

ተጀምረው የተከፈቱ ዋቂት መጻሕፍቱን እየዘጋ ቀሰላቸው።

ከሶስት ዓመት በፊት ከሚሰቱና ከውሰቱ መንትያ ልጆቹ ጋር የተነሡትን ፎቶ ከሰረጲዛው ላይ አንሰተ በጥንታቱ ማጤን ጀመረ። ወንዘሩን አሸክርክሮ ወደ መስኮቱ አመጠቀ ተመጠ። ደጅ ደጁን እያየ ፈዘዘ። አውን ፀሐይዋ ሙሉ ለሙሉ ጠልቃለች። ደንግዝግዝ ያለ የአመሻሽ ብርሃን ባካባቢው ላይ ተንሰራፍቷል። ዓይኖቹ በእንባ ገጥሞ ሲሉ የሚተናንቃውን ሳግ ለመቆጣጠር ምራቁን ዋጥ አደረገ። ፍተሙን ቀስ ብሎ ወደ አስተካከሉ አስቀመጠው። ጠረጲዛው ላይ ባፍጢሙ የተደፋ ሴላ ፎቶ አንሳና ለቅጽበት አይቶ ገለጠው። ጠረጲዛው ላይ በልጅነቱ ከአባቱ ጋር ሲላቱ የተነሡት ነው።

አባቱ ዋንቁት፣ ጽጹና ትንሀ ሠራተኛ እንደነበሩ ትዝ ይለዋል። ሰው ሁሉ እንጂት ይፈራቸው እንደ ነበር አውንም ዓይኑ ላይ አለ። በፖሊስ ኮሚሽንና በማዕከላዊ ምርመራ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሠርተዋል። አብዮቱ ሲፈነዳ የመቶ አለቃ ነበሩ። በአሥር ጊጀ ወደ ከፍተኛ ማዕረግ ከተሸጋገሩ ዋቂት ሙኮንኖች አንዱ ናቸው። በደጅ እንደ አገባብ አስፈሪ፣ እንደ መብረቅ አስደንጋጭ ቢሆኑም፣ እቤት ውስጥ ግን ተጨዎች፣ ደስተኛና ቤተሰባቸውን አፍቃሪ ነበሩ። የሁለትንታቸው ነገር ግራም ለርሱ ምስጢር ነው።

በደርግ ምትክ ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝ ነገሮች በፍጥነት ተለዋወጡ። መታሰሪቸውን ሲለማ ድንጋጤው ለረጅም ጊዜ አለቀቀውም ነበር። ከአሥራ ምስት ዓመታት አስራት በኋላ ነበር በጤና መታወክ ምክንያት የተፈቱት። ከእስር ቤት ወጥተው ብዙም ሳይቀየ ከዋቂት ወራት ሕሙም በኋላ አረፉ። ከሙሞ ታቸው በራት ለተወለኑ ሳምንታት ቢሆንም ዋሩ ጊዜ አብሯቸው አሳልፏል። ሰምቶ የማያውቀውን በደም የተቀባ ታሪካቸውን ያጫወቱት ያኔ ነበር። እስር ቤት እያሉ የጓቶችን ረጅም የማስታወሻ ደብዳቤ የሰጡት ያኔ ነበር። አሳዛኝና ዘግናኝ የኑሣዜ ትረካቸውን ባንበበ ቁዋር የሰላ ሰው ታሪክ እንጂ የደገተጫዋች አባቱን ታሪክ የሚያንብ አይመስለውም።

በሕሙና በእርጅና የወጻደቀ ሰውነታቸውና በሐዘንና በጸጸት የተሰበረ መንፈሳቸው ከፊቱ አይጠፋም። በዘያ የመጨረሻ ቀኖት ውሃ ቀድቶ ለመጠጣትና የገባ ሰውነታቸውን ደኅፈው ለመቀመጥ እንኳን አቅም አጥተው ነበር። በሰለለ ድምፃቸው ሊያወሩ፣ የሳሱ እጆቻቸውን ለማንቀሳቀስ ሲሞክሩ ያሳዩት የነበረው ሥቃይ ዓይኑ ላይ ደቅን አለበት። በደከሙ እጆቻቸው ጠንካራ እጆቹን ይዘው ከንደንጓዴ ዓይኖ ቻቸው ውስጥ የመጨረሻ እንባቸው በተሸበሸበ የፊት ቀዳዳው ላይ ክብልል እያለ የንጉሉት የመጨረሻ ቃል አይረሳውም። በእንባ የተሞሉ የራሱን ዓይኖች ጠረገ ጠረገ አድርጎ ወቃሚ ፋይሎችን ቀልር ከሚያስቀምጥበት መሳቢያ ውስጥ የርሳቸውን ማሰታወሻ አውጥቶ እሳቱ አጠገብ ሄዶ ተቀመጠ።

ደንገት የሆነ ያሳብ በአእምሮው ውስጥ ሽው ሲል ደንገጠ። ሃሳቡን እህቱ ናት ከነምገት በፊት በልቡ ውስጥ የዘራችበት። "በአባታችን ጸጸትና በትክክል ያልተኖረ ህይወት አዙሪት ውስጥ ራስህን አትክተት። የሁሉም ሰው የአደራ ሃላፊነት የራሱን ህይወት መኖር እንጂ በወላጆቹ ቀዳ ውስጥ ገብቶ የነርሱን ውድቀትና ጸጸት ማከም

አደንደም' ሮሚው ያሏ ትዝ አለው። ለመጀመሪያ ጊዜ በአባቱ የአደራ ቃል የታሰረ መሰሎ ተሰማው። ለሚቀን አልወደደውም። ደብዳቤውን ማንበብ ሲጀምር ከሚጠብ የሚጨነቅ ሆኖ ታየው።

አባቱ ያደረጉትን ስሁተቶችና ብሁ ጸጸቶች የሚገልጹትን የመጀመሪያ ነጥ አንድ ባንድ ያነበና ጭምድድ አድርገ ይይዛቸዋል። ከዚያም እጁ ውስጥ እንጂ ባለ የሁኗዘለሰለው ወረቀት ከሚነደው እሳት ውስጥ ሲወረውረው ቦግ ብሎ ይነዳል። ወረቀቱ ወደ እመድ ሲቀየር እንደገና የሚቀጥለውን ከፍል ማንበብ ይጀምራል። ጽሁ መጨረሻው ገጽ አባባቢ ሲደርስ የያዘው ገጽ ሥክ ብሎ ስራሱ ማንበብ ጀመረ።

'ልጀ ሌላ፣ አለ አባቱን አይደለሁም፣ ብፈልግም መሆን አልችልም። አንተም እኔን አባትህን ሳትሆን ሌላ ሰው ነህ። አባቴ ጭቁኖን ታሳ ፈንታው አደርን የሁተለበ ከስቀላ ጥሰኖ በገሬ ነበር። ትርውን ካምላክ የተሰመ ያርባ ቀን ለሮል ብሎና ተቀብሎ ኖረ። መወለዱም ሳይታወቅ በልጅነቱ አርጅቶ በድክመት እንደማቀቀ ምተና በተመለደበት ሰፈር ተቀብሮ ተረሳ። አለ ጸገም የኑን ፈለግ አልተከተልኩም። ገና በልጅነቴ ፅጣ ፈንታዬን በጀጀ አደረግኋት። 'የሕይወቴን ድርሻ ከማንም አልሰምንም፣ ሊከለለኝ የሚችልም አንዳች ሰው የለም' የሚል ጠንካራ እምነት ነበረኝ። ሆኖንም ልሸከር አይደለሁም፣ ለማንም ጊታ መሆን አልፈልግም ብዩ ለራሴ ማልኩ።

ከቅቱ አገር የሶንቀጠቀጠቸላቸውን የጻጀዝማች መክቴን ብኖሮ ልጅ የነበረችውን ያንተን እናት ያገባኋት ያለማንም እርዳታ፣ የለምንም ለመናና አቤቱታ ነበር። ፈተናው ቀላል አልነበረም፣ ያጋጠሙኝ መሰናክሎች ሁሉ ወደ ላይ ያወጡኝ መሰላሎቼና ቸኖው። መሰላል ያላደረከው ችሺ ብቻ ነው መቀበሪያ ገደል የሚሆንብህ። መፈቀርና መከበር ለምች የሚሉህ ላይሆን ቀቀረብክላቸው ማንነትህ የምታገኘው ምላሽ ነው። የፈለግሁትን አገኘሁ፣ ያሰብኩትን ሆንኩኝ።

በዚሁ ትኩስ የመጣትንትና የሰኬት ዕድሜዬ ላይ እኔና አብሮቱ አኩል ፈነፋን ብል ማጋነን አይሆንም። አብሮቱ የቾገረውን ሁሉ ነጻ የሚያወጣ የድሽት ማክተሚያና የጭቆና ማብቂያ ብቾኖ ነጻና ለመሆኑ የርግፊ አልነበረኝም። የኖ ትውልድ የሰሻሊ ዝምን ትርጮም ለማወቅና የኩሚኒዝምን ፋይዳ ለመረዳትም ሆነ ለመጠየቅ ደንታውም ጊዜውም አልነበረውም። አሮጌውን ማፍረሱ ላይ ሰንረባረብ አዲሱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ጥያቄና ሐሳብ አላስጨነቃንም ነበር። የተፈጠረው እንደ ኤሌክትሪክ የሚነዝር የሰውጥ ማዕበል ከነሙሉ ውብቱና ግሰቱ ለእኛ አዲስ የሃይማኖት ነፃ፣ የነጻነት ሥራ፣ የብልጽግና ጮዳናና የሞኑቱ ሕዝባችን ብኖና ብሩህ ተስፋ ሆኖ ታየን።

'ወዲያው ከውጪ ወረራና ከውስጥ ተቃውሞ ሲቀሰቀስብንና ከግራ ከቀኝ ሲያሚድፈን፣ የማያባራ ወታደራዊና አብዮታዊ ቀጣ በውስጤ

ተቀሰቀሰ። አየሁ ቀጣ ደግሞ ጨካኝና አብድ ያደርግሃል። የአብዮቱን መሪዎች የደመሰስን መሰሉን የአገሪቷን ምርጥ ልጆች ጨረስናቸው። ንጭ ሽብር አወጀብን ያልነው ጸረ ሕዝብ ኃይል በቀይ ሽብር አጋይተን ያሸነፍን መሰለን። ነገር ግን በድርብ የሽብር አሳት አንድ ትውልድ ፈጅተን ባዶ ቀር ታቅፈን ቀረን። አብዮት ሰሚባል ሐሳብ ከሁር ሰው አንደ ቅጠል ረገፈ። አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት በሚል መፈክር፣ ራሷን እናናት አገርን በሰመቃ ገመድ አንቃን ገደልናት። የልጆቿን ፊሳ በያደባበዩ ጥሰን የድል ጮዚ እየረገጥን ተሰደንባት።

የያዛትን ገጽ መጨምደድም አሳት ውስጥ ሰመጣልም አትም አጣ። ማንበቡን አደርሶ የቀሩትን ጥቂት ገጾች ከጉኑ ሶፋው ላይ አስቀመጠና ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደ። ፊቱን ሰበሰ ባለ ውሃ ታጥቦ ከመስተዋቱ ውስጥ ባለው የራሱ ምስል ላይ አፈጠጠበት። ጸጉሩና ጢሙ ማደግ ጀምሮ ሌላ ሰው ሳያስመስለው አልቀረም። በግዴ ፈገግ እያለ አጠጩን አሻሸ። የሰበሰውን የስፖርት ቱታ ጃኬት ሙሉ ለሙሉ ዘጋው። መነጽቱ አጠገብ እንደገና ቀሞ ይሄንን ደብዳቤ ማታጠሌ ልክ ነው አይደለም እያለ ወደ ቢሮው ተመለሰ። ወደ ዓር ከሚያሳየው ትልቅ መስኮት አንጻር ቁሞ ደጅ ደጁን እያየ አየጨላለመ ያለው ደጅ ላይ መልሶ አፈጠጠበት።

በዚህ መሃል አንድ ነገር ከፊቱ ካለው የመስኮቱ መስታወት ጋር ሲላተም ከሐሳቡ ነቃ። በዚያው ቅጽበት ከመስኮቱ ላይ ተንሸራታ ወደ ታች በትወድቅ ወፍ መሆኗን ነገ። በመስታወቁ በኩል ወደ ታች ሲያያት ቢሞክርም አልቻለም። የደጹ ብርሃን ይመጻብሽ ወይም በውሃ ልኩ አንጻር ካሱት አበቦች መሃል ወድቃ ተሸፕጣ ሊሆን ይችላል ብሎ አሰበ። መስኮቱን ሲከፍተው ከደጅ ያለው ቀዝቃዛ የንፋስ ሽውታ ፊቱን ሲገርፈው፣ የወርቹና የነፍሳቱ ሚጫታ ደምቆ ከጆሮው ሲዘልቅ ከገባበት ሐሳብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ነቃ። ሳያይ እንዳይረገጣባት እየተጠነቀቀ በመስኮቱ ዘልሎ ወጣ። ሳርና አበቦቹን እየገላለጠ ቢፈልጋትም ሊያገኛት አልቻለም።

በመጨረሻ ከእንድ ጥግ ላይ የሚንቀሳቀስ ነገር አይቶ ጠጋ ሲል በጀርባዋ ከንብል ብላ አገኛት። የምተች መስሎት አዘነ። ብድግ አድርገ ሲይዛት ትንሽ ተንፈራገጠችና አገጮን ሰብስባ የምተች ይመስል ጸጥ አለች። ዙሪያ ገባውን ቃኘና በመጣበት መስኮት ተመልሶ ገባ። በእጹ እንደ ያዛት ባንድ ጣቱ እያባበሰ የቁሰለች ወይም የደማች መሆንዋን ለማየት ሞከረ። የክንፏ ላባ ከመዘበራረቁ በቀር ምንም አላገኘም። እየደከመ ካለው እሳት ፊት ለፊት ተቀመጠና የበለጠ እንዳብሙ መረመራት። የክፋ ቁስለትም ሆነ ተሰፋ ሰጪ የሕይወት ምልክት ሰላላየባት የሚያደርገውን አጥቶ ከፊት ለፊቱ ወደ ሙቀቱ ጠጋ አድርጎ እስቀመጣት። ከሶፋው ላይ ያስቀመጠውን የተጀመረ የአባቱን ደብዳቤ እንስቶ ማንበብ ቀጠለ።

'አሁን ልቦናዬ ተመልሶ ሳስበው፣ ሕዝቦቿን ካልሆነ በእውነት አገር እንል የነበረው ምኑን እንደሆነ አይገባኝም። ልጆቿ ካለቁና ከተሰደዱ እናትነቷ ምኑ ላይ ይሆን ብዬ እንዝበገባለሁ። ዛሬ ያለፈውን ዞር ብዬ ሳየው የሚሰማኝ ብዶ ጨ ሽት ነው። የመፈክር፣ የሰብሰባ፣ የዘመቻና የፓርቲ

• 2 •

ሴላሙ አርብ ከሰአት በኋላው ከመቼው ፈጥኖ እንዳለቀ አልታወቀውም ። ከወትሮው ቁጥራቸው የበዛና ችግራቸው ውስብስብ የሆኑ ባለቀጠሮዎችን ሲያይ የሰ ። እስከናካቴው ካልቀረች ቢያንስ ማርፈዴ የተለመደው የዕለተ አርብ የመጨረሻ ሙሾተኛው እንኳ ሳትቀር ግራ በሰዓቷ ቀደም ብላ ደርሳለች ። ከጥቂት ወራት በፊት ባለሷ በማይውጣው የእጻ ማጥ ውስጥ ገብቶ በብስጭት ራሱን ካጠፋ በኋላ የገባችበት የልቅ ድብርትና የሐዘን አረንጓ ነበር ወደ ከሊኒኩ ያመጣት ። ብዙ ጊዜ ሞልቶላት በቀጠሮዋ ባትገኝም እሱን ማየት ከጀመረች ወዲህ ጥሩ ለውጥ አሳይታለች ።

ከአርቧ የማይለየው የሃምሳ አመት የመጨረሻ ልጁም አብሯት ይመጣል ። ከሴላሙ ጋር መሟቱና መላፋት ስለሚወድ ከርቧ ይልቅ ሳምንታዊውን ቀጠሮ በናፍቶት የሚጠብቀው እሱ ሆኗል ። ከፍለ ጊዜው አልቀ ከመሰናበታቸው በፊት ፒያኖ ለሚያሜተው 'ዶክተር ፒያኖ' የሚል ስም አውጥቶለታል ። እነርሱ ሲንጋተሩ እርሱም በፈናው አልፎ አልፎ ከራሱ ጋር እያወራ ፣ በሰጠው ባለ ቀለም አርሳስ ወረቀቱ ላይ እንዲቀባ የሰጠው ስዕል ላይ ይቸከችካል ።

የናው ክሊኒክ በሚገኝበት ቪላ ውስጥ ካሉት ሁለት ሰፋፊ ሳሎኖች አንዱ የርሱ ቢሮ ነው ። በጥሩ ሁኔታ የተሠራው የድሮ ቤት በተንጣለለው ግቢ ውስጥ በባሮች ተከቦ ሊወጣ የተዘጋጀ ሙሽራ ይመስላል ። ሰፊውን ክፍል መሃል አጋማሹ ላይ ያለው ከፊል ግድግዳ ቢሮውን ለሁለት ይከፍለዋል ። ባንድ በኩል የግል ሥራውን የሚሠራበትና አልፎ አልፎም እንግዳ ተቀብሎ የሚያናግርበት ቦታ አለው ። ከወደ ጥግ አካባቢ አነስተኛ ፍጅ፣ የቡና ማፍያና የውሃ ማጣሪያ ይታያሉ ። ከሥራ ጠረጴዛው በስተግራ ባለው ሰፋ ያለ ቦታ ደግሞ መጻሕፍት የተገጠገጡበት መደርደሪያ ግድግዳውን ሞልቶታል ። በአንፋሩ ደግሞ ተወዛዋዥ ወንበር ከትንሽ የነገ ጠረጴዛ ጋር ተመይሟል ። መተከሻና የምሳ ጣቢያዬ ነው ብሎ ሰይሞታል ።

በዚርው ሌላእጋማሽ ደግሞ ሁሙ ተኞቹን የሚያይበት ክብ ሠርተው የተደረደሩ ሶፍ ሶፋዎች አሉ ። ከፊቱ የተቀመጠችው ተመካሪ ስታወራለት ጭንቅላቱን እየነቀነቀ

ሙቢነው ውስጥ ገዐቶዲ በነምነው ቢሞክር ምተሩ አልነካሣ አለው። ችጉነነ ዩፎ ብሌ የዜስየሰው ብትሪ እንደ ሆነ ነዘየ ትል። ወደ እሷ ሲመጣ እየችና መስከቴነ ያቱ እደርጎ፣ "ምነው?" ብሎ ነው።" አለች፣ ያሰበን ለውሮ ሲቀር እንደማይደነን የሰፉ እደርጎቸ።

"አደ ሮጌ ... ብትሪው መሰለኝ፣ አልነክ አለ ምተሩ። ባንሪ ማንዲያ ገመቴ አለኽልንር"

"አዲ ... ልይተደሀም፣ ሽረ ምንም የለኘም። ታዲያ ምን ተሻለ፣ ሰምን ቢጌ ዘቢና አብረን ደርን ... ከራት ብንሄ ወደ ቤት እኒ ላደርስህ እችላለሁ" አለች፣ ለመሠረድ አይነት በሪን ከፍተ አንድ አንድን በከፈል እያጠጣች።

"አደ ነ... እስ ይሻላል መሰል" ብሎ፣ በረጅሙ ተነፈሰና ዞር ገነ። የምንነኣኒ ውስጢም ውጪዎም ብርማ የሆነ ቢ እም ደቢጢሙ ኢክስ ፋይፍ ስትሆን ውስጢም ንጹሀና ስመሳንም መንሃ የተመደች ናት። ጭባ በማያጣት በርሱ እርጌ የጥን ያደላክስ ስርኛ መቀለር ትውሰዋች። ሂልተን ለመኔድ ስለመስኑ ለመድረስ ብዙም ለልመደናቸውም። ከወደ ጥፃ እስካቢ ተቀመጡና የቢቀን ፒፃ አዘው ወደ መሬታችው ነው።

ያሰውት የፃ ቢመጣ ከመቀመጫው ተነሰና "እስኪ .... ጀምሪ አንቺ .... እኒ ብእኛ ስለምነ ታኮቢ መጣሁ" ቢል፣

"ግሌም ... ደርጋሀና ሙብቅያለሁ። እንዲያውም እስከዛ ማሚ ጋ ልደውል፣ ቢመጀ እንሂሳለህ" አለችና፣ ስልኳን ፍሌጋ ስርዓቸን መዘርዘር ጀመረች። ሒሴቷነ ሰከው ዮሞል ደምቀ ምንብ ቢ ቅም በዘኣተኛ ተጣቢል። ዝርብ ማታ ስመገቡ ደመመልል ሰሰከል ፊት ላይ ከፍ ያለ መንፈስና የጋል ስሜት ይንሸራሸራል። እየሰሉ ባስ የልሆኑን እያወሩ ቢማጭቱ ቀደ። በውስጢ ስለ እርሱ ልትወይቀው ያሰበችውን ኦዛይ እንዲት እድርን መጀመር እንዳልነበት ሲታሰብ ቀየችና፣

"እኒ የምልህ ሳስተር ሌላ፣ ካሜሪካ ተመልሰህ ከመጣህ እኮ በሶን ሥርጉቱዎ ቀው ብዙን አላወራንም። እንዲት ናቸው እኮ ንጹሕ" ብጪጨዎቹማ እንዲት እነዚ ናፈቁን ... ዶይ አንተ ግን ናፍቀውን እንዲት ነው የምት ችለው።" አለች፣ ፈዘነ እያሠናች።

ያሳውን የፒዛ ቆራጭ መልሶ ለስቀመጠና አምባ ውሃውን የንጨት አድርገ "እንሪት ነው የምችው፣ እውነቱን ልንገርሽ" ...አልችልውም። ግን ደግሞ ምነ ይፍረ'ኳ" ሶሰት ወሶ እያሠኘም። እንድ ነገር ለማድረግስትፈልጊ ሌላ ነገር መሥሞነት ሙት ሊይቀርም። የሶስቁለስ ሕይውት ስትኖረ ደግሞ እንዳንድ ነገሮች እነዚ እንኳሀሀቸው ነይሆን እነሱ እንደ ፈልጉት ስልሚዬፍ ጭባው ብዙ ነው። "ግድረሙ ለዘሚረሙ ጊዜ ሲሆን እንደሚሉት አዋህል" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ። ዋነዋ አምባ ውሃ የየሙን ዘርዋዮቹ ዘዋዮቹ እያሸከረከረ የሉሳብ አዙሪት ውስጥ ገባ።

አምባ ውሃውን እየሞላችለት፣ "ቀደ እኒ የምልህ ... በእሁት የሄድክ ጊዜ ንጹሕ ሰዓየሀ ሙርታህ ዝር የደከው አደደል? ... ወዲያው ደግሞ ኦልሞሰት በመለት ተመልሰህ መጣህ። ከመጣህ ጀምሮ ደግሞ በፍጹም የቀድሞውን አንተ አይደለህም። አዲስ የሆነ ነገር ወደም የተፈጠረ ችግር አለ' ማለቱ ልትነግረኝ ቦሞችል ከሆነ'ብላ፣ ጠረጴዛውን በክርናቸ ተደግፋ መልሱን መጠበቅ ቀጠለች።

"አዲ ... ኖ ... ይ ... ኖው ... ቀይ ምን ልንገርሽ፣ ነገሩ ራሱ እኒ ስመራ አይመችም። አኒይ ... አንዴ ባጠቃላይ ወደ እዚህ አገር መምጣቴንም ሆነ የህከምና ሥራዬ መከራቴን ... በዚህም የተነሳ አብሮኛው ጊዜዬን እዚህ ማጥፋቴ ልክ ነው ወይስ ልክ አይደለም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ትልቅ ትግል ላይ ነኝ። ንጹሕ ሁልጊም እዚህ መምጣቴንም ሆነ ከሊኒክ ከፍቼ መሥራቴን ለሰውጥ ብል እንኳን የቃየሁ ነገሮች ሉላው አስቸጋሪ ነገር ደግሞ ... አሁን ሀሳቤን ልሰውጥ ብሄድም ተመልሺ ብሄደም ለሰ ያሰው ነገርም ተዘለሻሽቷል። ስለዚህ እዚህ ብቀይም ተመልሺ ብሄደም ስውጥ የሰውም ። እስኪ እየበላሽ" አለ፣ በመሪው ትመምዳ መብላቷን አቁማ ስለነበር።

"ይሻሙ በሳው አኮ፣ እንደዚህ እንደ ራብኝ አላወቅሁም ነበር። እሺ ግን ቀደ በመጀመሪያ ... በእሁት እዛ የሄድክ ጊዜ ምን ሆነ?" አለች፣ ግራ መጋባቷ ጨምሮ።

"አኒይ ... በመጀመሪያ ነገሩን ሌላ ሰው እንዲያውቅ ስለማልፈልግ ሲራስሽ ብቻቷው። ትዝ ይልሻል ... የዛሬ ሰባት ወር ገደማ ከክሊኒኩ ምረቃ በኋላ የሄድኩ ጊዜ' ሁለት ቢት መኖር እንደማንችልና በምንም መንገድ እሷ እዚህ ኢትዮጵያ መሞታ መኖርም ሆነ ልጆቹ እዚህ እንዲኖድ እንደማትፈልግ ነግራኝ ነበር። ያው የተመሰነ የጨቃዋን መጨረሻ ላይ አማካይ የሆነ ነገር ለመፈለግ ተስማምተን ነበር ነገሩን የዚህው። በመሃል ዋሩ የተሻሻገኙና ልዩነታችንን ቀስ በቀስ የምንፈታው መስሎኝ ነበር። ግውን እኮ ነው የሚያችተው" አለና ትንፋሹን ያዘ እደረገ።

ሁሌም ውጥረት ሲሰማው እንደሚያደርገው እጁን ጨበጥ ፊታ አድርጎ ንግግሩን ቀጠለ። "ያው ባለቅኪይ እንድትመጣ ስትለኝ ለእኔ የመሰልኝ ወደ ልጆቹ ቃመው ወደ የሆነ ነገር ተፈጥሮ ነበር" ሲል፣ ቀጥል ብሚል ዓይነት ዓይናቸን እሱ ላይ እንደ ተከለች ጥንትላይን ንዶነቶች። "እና ገና ስደርስ በጣም ነበር የደነገጥኩት። መኝታ ቤት ስደት፣ ምን ልበልሽ ሁሉም ነገር አልቀ ነበር የጠበቀኝ። ባጭሩ የፍቺ መረቀት አደጀታ እንድፈርም ወየቀችኝ።"

"እኒ ለላ...ም...ንም እኮ" አለች ድንገጥ ብላ። አቄ የደረቀ ስለመሰላት ትንሽ ውሃ ተከጨች።

"ያ ... እኔም ሰማይ ምድሩ ነበር የዞረብኝ። ሌኒ ዊያስ፣ ምን አዲስ ችግር ቦረመር ስላት ያው በፊት የተነጋገርናቸውን ነግሮች እንሥታ "አንተም አባትህ በአውሀን እደራ ቶውባ፣ ደግሞም የልጅነት ፍቅረኛህን መፈለጥን ቀጥል። እኔም ራሴን እደውቅ አቅጣጫ ማስያዝ አለብኝ ምናምን ስትል የሆነ ነገር ካሰብኩት በላይ ከመሰመር መውጣቱ ዘደንገጥ የገባኝ ያኔ ነበር" አለና ወደ ጎላ ሲጠጥ ብሎ ቀቀመጠ።

"ከማለላቸዉ ብሎ ገበማንስቀ ተመልሺ ሰሄድቢ ታቸው ተቀልር ደረሰኩና፣ ወሰደች ሳዉወይቅ የጀዳበትን የሚነግረኝ እንኳ ሳላገኝ እንዲሁ ልቢ ተንሰፈነ የተቀለፈ በራችውም ላይከፈት፣ በዋያቁ እንደ ተሞላሁ ወደ እሚደካ ሄደኩ። ደጓ ደብዚዋ ብያ እስከ ሃፊም ሳትለየኝ ከኔ ጋር አለች። አልፍ ጊዜ ዶጋሚ ባከናዉ ሃፊም እንቀልሽ እንደ ሆንችብኝ አለች። እዚህ በመጣሁ ቱጥር ገትን ሰማንኝ ያላደረኩት ጥረት የለም። እስካሁን ገን ምንም ፍንጭ አላገኘሁም" ብሎ፣ ቢረጅ ተንፍሶ ዝም አለ።

"ብጣም ይገርማል ... ደብጻቤዋ ገን በዝህ ሁሉ ዓመታት ውስጥ እንኳት አልጠፋብም ወይም ተቀጻጻ አላለቀችም? ሁልጊዜም ቦርሳህ ውስጥ እንዳለ ነው የምትሃረው።" አለች፣ ሀዘንና መገረም ድብልቅልት ካለ ስሜት ጋር ውሳኔን አያተራመሰው።

"ኮርና በላን አድርጊ ቀሪ አስቀምጫለሁ። በታ ኦሪጂናሉ ግን ከእኔ እንዳለየ አልፈልገሙም። አይ ሶና ሰምን እንደሆነ ..." አለና መረቀቷን ተቀብሳት። በግንቃላ አጣጥፎ ከፊት ለፊቁ አስቀመጣት።

"ወይኔ ... ገን ምን ሆና ይሆን? የኔ ናት ስታሳገኘን" አለች። ሴላሙ ያልጠበቅችው አይነት ሴላ ሰው መስሎ ታያት። ጠንካራውና ሰሰው ሁሉ መፍ ያለው ሳይኪያትሪስት ሳይሆን ምስኪን በራሱ ዋያቁ የተሞላ ሆኖ አየችው። "ቀደ ገን ብታገኖስ ... ማለቴ አሁን ብታገኖት ምን ታድርጋለህ?"

"ምን አደርጋለሁ ... ሁ...ሀ ፍ...ፍ... ዚሲዮን ዋያቁዎች አሉኝ። እኒ እንጂ ሳንኖት ብቻ ይመስለኖል የማውቀው። መገመት አይቻልም" አለ፣ ሁለንተናው ጫ ንብቶት።

"እሺ እስክ ሣሬ እየጠበቀችህ ቢሆንስ ... ማለቴ ሳታገባ አንድ ቀን አገኘሃለሁ ብላ ተስፋ አድርጋ?"

ያላሰበው ዋያቁ ስለነበር፣ "እንዴ ... አብደሻል እንዴ፣ የምናወራው እኮ የ ብዙ ዓመታት ታሪክ ነው። የታይታኒክ ታሪክ በይው። አይመስልኝም። ከሆነም ... ያው ያለሁበትን ሁኔታ እንግራታለሙዋ። ጥሩ መንድምና እጎት የምንሆን ይመስለኛ አለ፣ ከዓይን ሥጋው ውጪ ያለውን ነገር በዓይነልቦናው ሰማየት እየሞከረ።

"እኔ ገን ሳሰበው ሳሰበው ... የምታገኖት ይመስለኖል" ብላ፣ ጠረጴዛው ላይ ተጣጥፎ ወደ ተቀመጠው ደብጻቤ እያየች ፈገግ አለች።

"አይ አንቺ ... እስኪ እንዳፍሽ ያድርገው። ኤኒ ዌይስ ... ይሄንን ሁሉ የነገርኩኝ ላለፅቅለሽ አልነበረም። ላንቺ የነገርኩሽን ነገር ለንጹሕ ስንግራት ነገሩ ቢያሳገኝትም ጉትን ፍሊጋ መነማቴን በዘነ አላየቻውም ነበር። በጓላ ላይ ሐሳቤ እንደማይለወጥና ይሆንን ነገር ካልጻፈው ሰላም እንደማይኖረኝ ስታውቅ እያንገራገረች ተሰማማች፣

"ዛሁት የጀድኩ ጊዜ ያለችኝ ነገር ግን ውሰጤን አውኮት ነበር። 'አንተ የልጅነት ፍቅረኖህን ፍሊጋ ላይ ታች በትል የኔ ሕይወት ተንጠልጥላ ልትቀር አትችልም። እነሆ

ፍቅሩን የሚያጋራኝን ቢጠፍን ያገኘው ይመስለኖል። ደንም የልጅነት ፍቅረኖህን ሳይሆን ልጅ እገር ፍቅረኖ እንዳገኘህም ሰምቻለሁ ... ምናምን' ስትለኝ መጀመሪያ ቀልጄን ዝር የመሰለኝ፣ ምክንያቱም ንጹሕ እንደዛ በአሽሙር የምታስብና የምትናገር ልጅ አይደልችም። አየዋየ ሳየው ግን ሁሉም ነገር የምሯን ነበር። ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ መሆናቸው ቀይቶ ነበር የገባኝ። አልና ፈቁን በሁለት እጄ ሸፍኖ ጸጥ አለ።

የምትሰው ሰለ ጠፋብት "አልገባኝም። አለችና ፊቷ ሁሉ የጥያቄ ምልክት መስለ።

"ልክ ነሽ፣ ምንም አይገባም። ሰማንኖውም እንዳልኩሽ ባሁት የሄድኩ ጊዜ ያጋጠመኝን ነገር ፈጽሞ አልጠበቅውትም ነበር። ምን ማድረግ እንደ ነበረብኝ እንኳን አላወቅሁም። በለዚህ ያለችውን ሁሉ አድርጌላት፣ የጠየቀችውን ፈጽሚላት፣ ከቆም በኃም ሳልኖር ቶሎ ወደ አዚህ ተመልሺ መምጣት ነበረብኝ። አይ ገስ ... አሁም ይመስለኖል ያበዘችውና ያለችው ነገር ሁሉ እውነት እንዲመስላት ያደረገው። እኔ የነበ ብጥብጥ የተሰማማችው።"

የሒሳብ ደረሰኙን ሲያነሳ እጄን ሲዘረጋ በፍዋነት ያዘችና፣ "እስኪ እጅዎት ይረፍ ዶክተር፣ ተጋዝሽ ነህ ዛሬ ረሳኸዉ?" አለች በፈገግታ።

ንጹሕ "ልጅ እገር ፍቅረኖ አገኝተሃል" ያለችው እሷን መሆኑን ሊነግራት አልፈለገም። አንድም ቅን ልቦናዋን ሊያቀሽሸው በላልፈለገ፣ ደግሞም ለንጹሕ ያላትን ትልቅ ፍቅር በሰሚያው። አብዛኖቹ ተስተናጋጆች ወጥተው ቤቱ ጭር እያለ ነው። ሰዓቱ አረት ከሩብ ይላል።

"ልጆቹስ ገን በናትህ?" አለች፣ ፊቷ እንደገና በሐዘን እየጨለመ።

"እም...ም ልጆቹን ...ምንም ማድረግ አልችልም ለጊዜው። ያው ፍርድ ቤት ብንሄድም ሰሲ ነው የሚሰጡት። በዛ ላይ አቅሙም ልቡም የለኝም ከንጹሕ ጋር ፍርድ ቤት ለመቆም። ለነርሱም ከሲ.ው ጋር ቢቀዩ ነው የሚሻለው። በታ ራሴን ብቻ ነው ይዤ የወጣሁት። ለዛውም የእኔም ግማሹ የት እንዳለ አላውቅም። የሆነ የማላውቀው ሴላ ሰው የሆንኩ ያህል ነው የሚሰማኝ"

"ሴላሙማ ነህ፣ ተጠራጠርክ እንዴ?" አለች ሳቅ ብላ አይን አይኑን እያየች። ጠረጴዛው ላይ ያለውን እጁን በእጇ መታ መታ አደረገችና ከሰልኳ ላይ ሰዓቷን አየት አደረገች።

"ይሁንእስኪ" አለ ያደገ ጢሙን እያሻሸ። "አይ ቲንክ፣ መንቀሳቀስ ላይኖርብን አይቀርም። እንዳይመሽብሽ እንጂም። " ለአስተናጋጇ የምትሰጠውን ትርሻ አስቀርታ መልሷን ወሰደች። የገንዘብ ቦርሳዋን ከሞናው ቦርሳ ከተቶችና ተነሡ።

"ሴላሙ አሉ ... ያለ ምክንያትም አልመሰለኝ ይሄንን ግራ የሚያጋባ ሰም ያወጡልኝ"

"ስምን መላእክት ናቸው የሚያመጡት በሚለው ትስማማለህ ማለት እ... መላእክት ደግሞ አይሳሳቱም" ብላ ላቀች አፏን ጠመም አድርጋ ። ከገጹን ይዛ ሚሳቅ እያየተካከለች ቀና ብላ "ጎን ማነው ስምህን ያመጣልህ?"

"የሰምኮኩ መልአክ ኮሱኔል ዳንሳ ናቸው ።" ከኔ የተሰየ ታሪክ አገኣናኒ ስለምፈልግ ነው ይለኝ ነበር ። እኔ እንኛ፣ ምን ዓይነት ሴላ ሰው ሆኜ እንደ ተገኘሁ በሰፉ ሰፊ ሰጥ መሀል አዋርጠው ወደ ውጪ ለመው-ጣት በዝም-ታ መራመድ ቀጠቱ፣ የሰው ንሰም መልአክ ነው የሚያመጣው የሚለው-ን አባባል እያሰበ ያገዳገድ በምችኩ ትሽ ቢለው ፈገግ አለ ።

መኪናው ፓሲፖርቡ በፍን ከፍታለት እንዲገባ ሰትይዝለት ሣት ብሎ ፣ "ኦህዮን ኤ ጀንትል ሌዲይ! ራቁ ሳያኽኝ ደግሞ በር ተከፍቶልኝ ... ታንክ ዩ" ሲል ፡ እየሳቀ ሃራ ገባ ።

"ታው ታለሀ፣ ብዙ መንዶች ሴት በር ከፍታ ልታስገባቸው ብትሞክር ለራሄ ኩ- የሚሉት ። ሊቸን ታጋብለው ሴት ሰትከፍል የማይመቻቸው- ወንዶች ብሁ ናችው- አለች ፡ ዮር ብላ እያየችው ።

"ለምንልደ ...በተከበሩ አካኪ ዘራፍ ማለት...? ግን ደግሞ መቼም ታው-ቂያዪ፣ አንዳንድ ሴቶችም ለንገር ብለው ካደረጉት ቀላል ላይሆን ይችላል ። ለእኖ አገር ወነድ ደግሞ ነገሩ ለምን እንደሚከብድ መረዳት የሚያቅትሽ አይመስለኝም።"

"አይ ባለሀ ... የኖ አገር ወንድ፣ የሴላ አገር ወንድ የሚባለው- አይገባኝም ። ሌት ልጅ እጄ እስክትገባ የመኪና አይደለም የሰማይ በር ለመክፈት አይመስለም ። ማክሲ የሴለው-ን ሜማ ተፈታብሽ ካላሰርኩልሽ እያለ ሲያሽረግድ ይቀይና ልክ የፈለገውን ሲያገኝ ደግሞ ውታ ቃጠን እየር ወፈረ እያለ መሳደብ ማመናጨት ይጀምራል ። ሳይነ- ሴት ሰትጋብለው ወይም የሆነ ትንሽ ትዕቢቱን ነካ የም ታደርግ ነገር ሰታደርግለት በደጀታ ወይ ቢያንስ በጸጋ የማይቀበል ወንድ ውሰ አድሮ ያከብራታል ብዬ አላም ንም።"

"ነጥብሽ ይገባናል ። ግን ደግሞ ገና ነን፣ እንደ ማኅበረሰብ ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል ። ከልጅነታቸው ወንድና ሴት ልጆቻችንን ከምናሳድግበት መንገድ ጀምሮ፣ ባህሉና ልማዱ የተጠላሰፈቡትን ማኅበራዊና ሥነልቦናዊ ገመድ ማፍታት ቀላል አይመስለኝም" አለ፣ የተደመመ ስልክ መኖሩን ለማየት ስልኩን እያወጣ ።

"ባለፈው፣ ከሲራክ ጋር ለቡና ስንወጣ እኔ ነበርኩ የነዳሁት ። ልክ እሁን ላገሰ እንዳደረኩት ከፍቼ ይሸለት ግባ ብለው፣ ዘራፍ አሻፈረኝ 'ምን መሰዬ ታየሽ ብሎ እ-ማ-ዬ ት-ሙ-ት እምቢ አሻፈረኝ አለ ። እኔማ ሥቂም አላባራሁ ። እሱ ደግሞ የዛነ አናደደው- ። ብቻ እንዲያው- ትዝ ስላለኝ ነው-" ብላ ሣቀች ። ሲራክ አብሯቸው የሚሠራ ውጣት የአእምሮ ሕክምና ዶክተር ነው ።

"ምን መሰለሽ፣ ባህልና ልማድን መቀየር ቀላል አይደለም ። ሁላችንም በጊዜ ለገባነው ልማድና የቀደመው ትውልድ ፈልስፎ ለሚነብን ወግ ባሮችና አስረኞችሃ

አለ፣ የመኪናውን ቀበቶ እያሰበቀ ። በገፍ ላይ ትንሽ ካወሩ በኋላ ከብሔራዊ አስከሬሽኑ ደረስ ሁለቱም በየራሳቸው ሐሳብ ውስጥ ገብተው በጸጥታ ተዋለ ።

"ስለዚህ ...ታዲያ ምን እያስብክ ነው-?" አለችው ድንገት ዞር ብላ ።

"ምን እያሰብኩ ነው? ምን የማላስበው ነገር አለ ብለሽ ነው- ። ብዙ ነገሮች እኔን አሰጠቁ እንደሆነ አውቃለሁ ። አይ ዶና፣ ምናልባት የመጨረሻ ሙሳኔ ከማድረጌ በፊት ሁሉንም ነገር እገደገና ማየት ሳይኖርብኝ አይቀርም" አለ ከኪሱ ሙሰኖ የሚሙዝውን ስልክ እያወጣ ። "አህ እናቴ ናት መሰለኝ ... ቀይ እንዴ ልመልስላት" አለና፣ በአሥር ደቂቃ ውስጥ ቤት እንደሚደርስ ነግሯቸው ዘጋው ። እናቱ እርሱ ቤት ከሌሽ አይተችም ። ዝርዝር ጉዳዩን ባያው-ቁም ትዳሩ ላይ ያለው-ን ችግር ከእህቱ ስለ ሙ-ገራቱ ተወጥረዋል ።

"ቀይ ግን ዶክተር ሴላ ... ግኑትን ፈልገ ለማግኘት ንጹህንና ልጆችህን ማጣቱ ተገቢ ይመስልሃል? ማለቴ ... በንጹህም ቦታ ሆኜ ሳስበው- ነገሩ ቀላል አይመስለኝም ። ይቅርታ ግን .. ያለህበት አጣብቂኝ ስለማይገባኝ አይደለም" ብላ ነዳጁን ሰጠት አድርጋ ፍጥነቷን ጨመረች ።

"እኔ ኮ ግኑትን አገኛለሁ ብዬ ስነሳ ንጹሕን አጣለሁ ብዬ አይደለም" ሲል ዞር ብላ ገራ በገባው ፊት ስታየው ዝም አለ ። 'እውነት ታዲያ ምን ፈልጌ ነው-?' አለ በውስጡ ። 'እኔ የምፈልገው ግኑትን በተመለከተ አንድ የሆነ ፍጻሜ ማግኘት ነው- ... ይሄ ደግሞ ለምን ንጹሕን ሊያሳጣኝ እንደሚገባ ነው- ያልተረዳሁት ። "

"እሽ ግኑት ካልተገኘችስ? ወይም ብትገኝስ? ደግሞ ያባትህ አደራ ያለበትና በውስጥህ ታምቀ የኖረ ሀልሙሀና እዚህ ማድረግ የምትፈልገው- ነገር ከገነባኸው- የግልህ ህይወትና የኑሮህ አቅጣጫ ጋር ሲጋጭ ምርጫህ ምንድነው-?" ስትለው ። ትከሻው-ን ሰብቆ አጹን ጨበጥ ሰቀቅ እያደረገ ዝም አለ ።

"ዩኖው ሚስጥር ... አሁን የኔ ህይወት በሚገፋፋና በሚሳሳቡ ኃይለኛ ማግኔቶች መካከል እንዳለች ቁራጭ ብረት ግራና ቀኝ እየተጎተተች ነው ። ለየትኛው-ም ጥያቄሽ መልስም ሆነ ስሜት የሚሰጥ ማብራሪያ ማቅረብ አልችልም ። አሁን ለምጫወተው- የሕይወቴ ሙዚቃ የተጻፈ ኖታና የተስተካከለ ቅኝት የለኝም ። በቃ ምን ልበልሽ ... አለ አይደል ... ቀለም ባለቀበት ብዕር የምጽፍ ያህል ነው- የሚሰማኝ ። " የምትመልስለት ስላልነበራት ዝም አለች ። የሴላሙው- እናት ቤት ደሸፍ ሲደርሱ መኪናው-ን ዳር ላይ አቆመች ።

"በይ እስኪ ... በጣም መሽቷል፣ ገቢም አትባይ ። በጣም በጣም ነው- የማመሰግንው- ። እንዴት ቅልል እንዳለኝ ... ያው የቴራፒ ሒሳቡን እዛው- በክሊኒኩ በኩል እናወራዳለን" ብሎ ቀስደና ወረደ ። እሷም ወርዳ ጥምጥም ብላ አቅፋ ተሰናበተችው ።

እንም ሰማሁ ደስ ብሎኛል። አይዞህ ... ሁሉም ነገር በጊዜው ይፈጸማ
ለሁሉም የራሱ መንገድ አለው። ጊዜ የማይፈታው ቋጠሮና የማያስረሳው ነገር
የለም ትል የለ ረዘሙ አለች። ወደ መኪናዋ ገብታ አየሪቹውና ሙዚቃውን ጨምሮ
አብርታ ሮጦች። በፉ ሲከፈትለት እጇን አውለብልባ ወደ ሽከርከሪ ተፈተለከች።

ክፍል ፱

ድልድይ

• 3 •

ሴላሠው በአሙሮላኑ ውስጥ ሰውነቱን እያፍታታ ወዲያ ወዲህ ሲል ሳየ፣ እንቅልፍ እንዲወሰደው ፈቀን ሽፋፍና ደገፍ ብሎ ተቀመጠ። ረዳት አባፊረቁ "አዲስ አበባ ለመድረስ የቀረን አምስት ሰአታት ሲሆኑ የምንደርሰውም በባት አንድ ሰዓት ከሩብ አካባቢ ነው። የአዲስ አበባ የአየር ሁኔታ ..." እያለ የጉዞ መገለጫ ሲነግ 'እፍ ... ኧ ...' አለ ሰራሱ። አብዛኛው መገደኛ በየመንበሩ ላይ ያሸለበው ይመስላ፣ ብለቁ ንጹህና ውለቱ መንትያ ልጆቹ ግን ሰሽ ብለዋል።

ልምስቀንሰዓት ተሱ ለመጨረስ ጊዜም እንደ ዮታ በወደዱት አቅጣጫ ሰንነፋ የሚጀፉት እውነታ ቢሆን ብሎ ተመኘ። የጊዜ ላይ ጉዞ በተወሰነ ፍጥነት ያንደኛ የወደፊት ብቻ መሆኑን ሲያስብ ሰው መሆን፣ የጊዜ አሰሪኛ መሆን ነው ብሎ ደመደመ። በጊዜ ጉዳይ ያለውን ሃሳብ እያሰፋና እያጠበበ ሲያወጣ ሲያወርድ ቀየ።

'ጊዜ የዘላለም አሸከር ሲሆን፣ ሰው ደግሞ የጊዜ ባሪያ ነው። ሰው ኒነ በደቂቃና በሰዓት፣ በወራትና በዓመታት ሽንሸና፣ ክግድግዳው ላይ ሰትሱ በእጁ ሃያ ጠፍር ሲገሠው ሲቀጣጠረው ይሞክራል። ጊዜ ደግሞ ሰውን ክልጅነት ወደ ሙጭነት፣ ከጉልምስና ወደ እርጅና እያከለፈለፈ ከሞት ደጃፍ ያደርሰና መቃብር ይጨምረሃል። በክረምትና በበጋ፣ በጸደይና በመጸው እየተመሰለ መልኩን እየቀያየረ ሲመጣና ሲገፈ ሲሞርና ሲፈራረቅ፣ ... የጊዜ ጉዞ ያሁሪት እንጂ የወደፊት አይመስልም። በድስ ፈርነ ላይ ተቀናጦ በስኪትና በውድቀት፣ በቀጠሮና በድንገት፣ በጥበቃና በጥድፊያ ተጠቅ የሰውን ዕጣ ፈንታ የሚወስን ጊዜ መሆኑን በቀላሉ እንዘነጋለን። ጊዜን መግዛት ሲሰ ራስን እንጂ ጊዜን ማስገዛት አይደለም።

'በጊዜ ውስጥ ትናንት የትዝታ፣ ነገ ደግሞ የተስፋ ጉተራ ናቸው። ካምሳ ትናንት ... ያልመጣ ነገ ይሻላል። በእጅ ያለ ዛሬ ግን ከሁሉም ይበልጣል። ዛሬ ሰአያ ያለ እየመሰለ የማይደንም ... ተመልሶም የማይመጣ ... ላንድ አፍታ ለቅጽበት ታይተ ጸርቆ ከሌለው የዘላለም ጠፈር ንብቶ የሚሰወር ... በትናንትና በነገ መሃል የተሸነፈ እንው ነው። የዛሬ ምስጢሩና ጥልበቱ ያለው ደግሞ 'አሁን' ላይ ነው። 'ቅድም' እና 'ነኋላ' ግን ያለቦታቸው ባፈ ውስጥ የተደነቱሩ የትናንትናና የነገ ሽርፍራፊዎች ናቸው።

'የሰድሜ ባለጸጋ የሆኑ ጨቅላ ሕፃናት ካልተነካ ቁባ ዕድሜያቸው ላይ ብዙ የፈቃዎመና ከሞሞሱ በስተመጨረሻ በጸጸት የተምላ እርጅና ኩሲ መሆናቸው እይቀርም። የጀምት ጨዋታ፣ የመጣትነት ፍቅር፣ የጉልምስና ስኬትና የእርጅና ምገስ በሞናንት የሰፈ ሰድል ፍሬዎች እንጂ የነገ ተስፋ ወይም የትናንት ትዝታ ውጤቶች አይደሱም።'

ከተሳፈረበት ምዓብ ሲመጣ 'ጊዜም እንደቦታ ደርዘ ብዙ የህይወት እውነታ ነው' የሚል ባንድ መጽሀፍ ላይ ያነበበው ድንቅ አረፍተ ነገር ትዝ አለው። ሃሳብ እንዴ በጊዜ ውስጥ መጻያ ወዲህ የሚያንጉጥዘን አውሮፕላን መሆኑ ሰመጀመሪያ ጊዜ በራሰት። ቀና ብሎ ቅንሽ ተንጠራራ። አሁንም በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ያሱትን ሚስቱንና ልጆቹን አየና 'አያ ... ውሉተኛው በጊዜ ውስጥ መንሸራሸሪያ አውሮፕላን ደግሞ እንቅልፍ መሆኑ ነው' ብሎ ፈገግ አለ። ሰው በምናቡና በራእዩ በጊዜ ውስጥ ወደ ፊት ይጓዛል። በትዝታውና በትውስታው ደግሞ ወደ ኋላ ሲንጉድ ይችላል።

ከብዙ ማዝባባትና ማላመን በኋላ ነበር ባለቤቱ ንጹሕ ልጆቹን ይዘው ወደ ሀገር ቤት ሰምስት ወር እረፍት በመሥጣታቸው የተስማማችው። በልጅነቷ ከሃገር ቤት በጣች በኋላ ሳጭር ጊዜ ከወላጆቿ ጋር ካልሆነ መጥታም አታውቅም። የመጨረሻ ንዞዋ ከአስራ አምስት አመት በፊት ነበር። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ይሰሩ ከነበሩ አባታቸው ጋር ካገር አገር ሲንዙ ሰላደት፣ ምንም አይነት ረጅም ጉዞ አትወድም። ወደ አዲስ አበባ ለመድረስ ሲቃረቡ የአውሮፕላኑ የውስጥ መብራት ሲበራ ነቃች።

"ደረስን እንዴ ሴላዩ?" አለች አይኗን እያሻሸች ፊቷ ላይ ጣል ያደረገችውን ያንነት ልብስ አጣዋፋ ክነኗ እያስተመጠች።

"ኦልምስት ... አንድ ሰዓት ነው የቀረን፣ ትንሽ ተኛሽ?"

"ያ ... እንደ ነገሩ ... ያውሮፕላን ውስጥ እንቅልፍና ምግብ እኮ ..." ብላ ሳቅ አለች፣ እጇን እያሻሸ ፈገግ አለ። ብዙም ሳይቀይ ልጆቹም ነቁ። ለፊት ማጽጃ የሞቀ ርጣ ሲሞር አሲ ልጆቹን ይዛ ወደ መጸዳጃ ክፍሉ አመራች። አውሮፕላኑ መሬት ሲነካ መንገደኛው ሞብዜባና አልሊታውን አቀለጠው። ነገሩ ባይገባቸውም ልጆቹም አብረው እያጨበጨቡ ሥው። ነገሩ ግራ ያጋባት ንጹህ 'ምንድነው በሚል' ጥ ያቂ የኮሞላው ፊት ሰታየው።

"ከሰማይ መውረድ ቀላል ነገር ነው እንዴ?" ብሎ ሲስቅ፣ ቀልዱን እንደሆነ ገዘቷት።

"የምር ..." አለችው።

"የእርይታ ይሁን የደስታ ... የምሲጋና ይሁን የአድናቆት እኔም አይገባኝም። ስሚቀንግን አልጠላውም" አለ፣ የልጆቹን ልብስ እያስተካከለና የአጅ ሻንጣዎ ቻቸውን ከራሰ በላይ ማስቀመጫዎቹ ውስጥ እያወጣ።

"ጎን ማለት ነው።"

"ይመስላል" አላት፣ በረጅሙ እያዛጋ።

"ወይኔ ... ካሁኑ አሜሪካ ናፈቀችኝ" ስትል፣ ከጀርባዋ ያሉ ሽምገሌ ያሉ ጓደኞቿ በሚያደርጉ እይታ ዝርሚታችና ጥንቅሳታቸውን አመሳመው።

"ከሳት መር በጓሳ በንሥለስ ደንም 'መቼ ነው ኢትዮጵያ የምንመለሰው ...' ባልጄና ናፈቀችኝ ማለትሽ አይቀርም።" የሊሚገፌሽን መስኩቶፍና የንሥሳ፣ ፍተሻውን አልፈው ሲመጡ ደካምና ገራ መጋባቷ ፊቷ ላይ ይነበብ ነበር። የልጆች እጅ ይዶ ከፊቷ የሚሄደውን ሴላሙውን እያየች ከገኗ እቃችውን የሚጓጓዝ መጣት በተሰላቸ ድምጽ፣ "ሴላም ፍተሻ አለ እንዴ?" ስትለው፣

"አይ ቢቶ ... የሚመሰጻችው መኪና አላችሁ?" አለ፣ ዞር ብሎ ከላይ እስከታች እያጤናት። ካለንገራና ከዋያቁዋ ለረጅም ጊዜ ውጪ የኖረች መሆኗ ገብቶታል።

አርጌ አየር ማረፊያ ሰፈር የሚገኘው የሴላሙው እናት ቤት ነው ያረፉት። ሴፊና ሁሉም ነገሩ የተሟላ ስለሆነ በቂ ምቾት አለው። ገዥሕ በመጀመሪያዋ ሳምንታት ምንም ሳትደሰት ጊዜው እንደሞዛ አለፈ። የእንቅልፍ መዛባቱ፣ የምግብ ለውጥ፣ የልጆቹ ጤና ማጣትና መሰላቸትን ጨምሮ ብዙ ነገር አታከታታል። ለሎሙ ደንም ብዙም ሳይቀይ ጸውሱሰ ሆስፒታል ገብቶ መሰራት ስለጀመረ ብቸኝነቱም አልኖ ብሏታል። ቀስ በቀስ ጎደኞችስታፈራና ውጣ ውጣ ማለት ስትጀምር ትገሽ ቀለል አላት። ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ እንኳን ሊናርባት የሚመጣባት ሀገርም ሆና አልተዋጠችላትም። የሴላሙውና የልጆቹ ደስተኝነት ለምስጠር ፈጽሞ ሊገባት አልቻለም።

"ደስታ በሁሉም ቦታና ጊዜ ሊፈጥሩ የሚችሉት ነገር ነው ወይስ ቦታና ጊዜ እየመረጠ የሚከሰት እድል? ሰው በምርጫው ደስተኛ የመሆን ነጻነት አለው ወይ? ደስታ እንዳሻው የሚከሰት የእድለኞች እጣ ፈንታ ነው?' ለሚሉና መሰል በውስጥ ለተፈጠሩ ጥያቄዎች መልስ አላገኝችም። 'በቀላሱ የሚደሰቱ ... በሁሉም ቦታና ሁኔታ ደስተኛ መሆን የሚችሉ የተባረኩና የሚቀናባቸው ሰዎች ናቸው' ብላ አሰበች። 'ደስታ የኑሮ ምቾት ውጤት ነው ወይስ የሕይወት የትርጉም ፍሬ? ለመደሰት የፈለኸውን ሁሉ ማግኘት ያስፈልገናል ወይስ የሚያስፈልገንን ነገር መረዳትና ያለንበትን ሁኔታ የመቀበል ጸጋ ይበቃል? ደስተኛ ለመሆን ፈለገች።

ክፍል ፫

ሰዎቹ

• 4 •

የወዋቱ ሜሜታ ጋብ ያለለት ክሊኒክ፣ ድንገት አንዳች መአት እንደ መሳ
ድብልቅልቁ ወጣ። በደማቁ የምትመሀአንዲት ሴትና በዛ ያሉ አሻቢ ድምፆች የፈጠሩት
ሁከት የሁሉንም ቀልብ ሰቢል። የጸውሰሰ ሆስፒታል የአእምሮ ሕክምና ከሊኒክ ሀ
የውሰዋ ግድግዳ አንሳን አንባርቀው በትሮውንም ድምፅ የመከላከል አቅሙ እንደ
ነንሩ ነው። ክሊኒኩ ከየናው ሆስፒታል በሰተጥሮሮ ወሽቅ ብሎ ይገኛል። አንላይ
ያህል ከተራረፈ ዕቃ የተመራ ይመስላል። ዓይንና ዋርስ፣ ጆሮና ጉሮሮን ጨምረ
አእምሮና ካንንት በላይ ያሉ አካላት መታከሚያ ክፍሎች የሚገኙት በዚችው አነስተ
የሆስፒሊታሉ ምራቂ ቤት ውስዋ ነው። ካንንት በላይ ላለ ስውር ሕመም ሽነዋ ያላ
ቦታ መች አክችው ለማለት ይመስላል።

ሐዋት ረፋዱ ላይ ከሰው ብዛት የተነሳ በቢሮዎቹ መካከል ባለችው ጠባቧ ንራሪ
መተላለፉም ሞንቅ ነው። ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሰው ተስተናጋጅ አስታሚና
አሻቢ ነው። አንዳንዱ ዋቂት በከፍተኛ ደረጃ የታመሙ የአእምሮ ሕመምተኞ
ካሉ፣ አካባቢው በእሪታና በሁካታ ቀውጢ ይሆናል። ከቀኑ ስድስት ሰዓት ከመነ
በፊት አብዛኛው ሕመምተኛ ታክሞ ወደ የቤቱ ስለሚሄድ ሁሉም ነገር እንደገና ይ
ረጭ ይላል። በዚያ ሰአት ወዲያ ወዲህ ውር ውር የሚሉት የጽዳትና የካርድ ክፍ
ሠራተኞች ካልሆኑ እምብዛም ሰው አይኖርም።

ሌላው ቢሮው ውስጥ ሲያያቸው የቀዩትን በዕድሜ ጠና ያሉ ሕመምተ
ለማስናበት በሩን ሊከፍት፣ ከደጅ የቀለጠው የጨኸት ወላፈን ጆሮ ግንዱን ገረፈው፣
የክሊኒኩ ኃላፊ ነርስ ወደ እርሱ እየመጣች ስለ ነበር ተከታትለው ወደ ቢሮው ገቡ።

"ምንድነው ሜሜታው፣ ሲስተር?" አለ፣ በሩን እየዘጋ ፊቱን ወደ እርሷ መልሶ።

"ምን ሰላም አለ ብለህ ነው፣ ዶክተር። ፖሊሶች እንዲት አስቸጋሪ ላይኮስ
ሀመምተኛ አምጥተው ከቍጥጥር ውጪ ሆናብናለች። ሐኪሞቹ ሁሉ ስዕዘ
ብለው ቀደም ብለው ወጥተዋል። ነፍስ ጡር ስለ ሆንች ሳትታይ መድኃኒት ልሰጣ

አልፈለግሁም። እንዲያው ባክህ ብታይልን ብዬ ነበር" አለች፣ ቀልቧ ከውጭ ባለው
ሜሜታ እንደ ተሰረቀ።

"ምንም ችግር የለም፣ አያታለሁ። ከዚህ በፊት እዚህ የታየች ሕመምተኛ
ናት እንዴ?" አለ፣ መረጃዋው ላይ የተበታተኑትን የህመምተኛ ካርዶች ለማስተካከል
እየጠከረ።

"አዶ ... እኔ እንጃ፣ እዚህ እንኳ ታይታ የምታውቅ አይመስለኝም። ግን ክሮኒክ
ነርናት፣ የለየላት ጨርቂን ጥላ ጦጻና ላይ የውጣች ዓይነት ትመስላለች። መንገድ ላይ
የሎሙ መኪናዎች መስተዋት ሰባብራ መስለኝ ፖሊስ ማዚያ አሳድሪዋት ሲያቅታቸው
ወደዚህ ያመጪት። በዛ ላይ ደግሞ ድርስ ነፍሰ ጡር ናት። አይ ዘንድሮ እንዲያው ሴት
መሆን፣ አሁን እንዲያው በፈጣሪ ... ካልጠፋ ሴት ይቺን ምን ብለው ነው፣ ዘንድሮ
ወንዱም እንስሳ ሆነ መስል ልጂ፣ ምን ዓይነት ዘመን ላይ ደረስን አሁንስ፣" አለች፣
ሰመንገሸገሽ ፊቷን አጨፈራም ታ።

ለድሜዋ ለበድሳ ብዙም ያልቀረው ሲስተር ዘቢባ ለብዙ ዓመታት በአማኑኤል
ከማ በጻውሰሰ ሆስፒታል ሠርታለች። በልምድም በእውቀትም ከይረጁና ሙያውን
አውንም በፍቅር ከሚሠሩ ዋቂት የቀዩ ነርሶች አንዱ ናት። የምታደርጋት ዋቁር
ሳስማያዊ ፍሬም ቀሚን የእይታ መነጽርና ሁል ጊዜም የማይለያት ነጭ ሂጃብ ከጠይም
ከወፈፊቷ ጋር የተጣጣመ ነው። የምትነግረውን እያዳመጠ ያያቸውን ካርዶች ባንድ ላይ
ቀለላቸው።

"ምን ታደርጊዋለሽ ... ስዉ ብቻ ሳይሆን ጊዜውም ነው ያበደ የሚመስለው።
መንገድ ላይ ለሚኖር ሰው ደግሞ መቼም ቢሆን ሕይወት እብደት ናት። ቀይ ፖሊሶቹስ
ቢሆኑ አያስቡም እንዴ? እንደዚህ የተረበሸች ከሆነች መጀመሪያው ጎስ እንዴት ወደ
ፖሊስ ማዚያ መስደው ያሳድሯታል? ምንም ቤተሰብ የላትም ማለት ነው?" አለ፣
ሰውነው ሀመምተኖዋን እንዴት ብሎ እንደሚያናግራት እያሰበ።

"አይ ዶክተር ... አንተ ባሜሪካው እያሰብክ ነው። እዚህ አገር እኮ ብዙም
መላ ያለው ነገር የለም። በቤተሰብም መፍረድ ይከብዳል። ያንንም ይሄንንም ብሎ
ብሎ ሲያቅተው በቃ በየመንገዱ ወድቀው ይቀራሉ። ፖሊሶቹስ ቢሆኑ ከሌላው ሰው
በምን ይለያሉ ብለህ ነው። የተለየ ትምህርት ካልተሰጣቸው ምኑን ያውቁታል?
እንዲያው ተወኝ ባክህ፣ ሁሉም በደመ ነፍስ ነው" ብላ፣ ውጪ ያለው ሜሜታ ሲካረር
ተከታትለው ወጡ።

ካልሄድኩ እያለች ከፖሊሶቹ ጋር ከምትጉዋተተው ረጅም ቀጭን ሴት ጋር ፊት
ለፊት ተጋፍጠው ባሉበት ቀሙ። ሆዷ ተቀብትቶ ነፍሰ ጡርንቷን ያሳብቃል። ተሽራርቦ
ወደ ብዙ አቅጣጫ እንደ ቀንድ የተንጨበረረው ጸጉሯና እንትልፍ ሳይዘርባቸው
የከረሙ በርበሬ የመሰሉ ሕይወት አልባ ዓይኖቿ ጋኔኖች ስክረው ሲጨፍሩባት ያደረች
አስመሳይ ነበር ከመጮሁዋ የተነሣ የተዘጋው ድምፅዋ ጮርንና በፍጥነት ስታወራ
የምትሰውን ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። የሆነ ነገር ትለፈለፍ ትለፈለፍና ደግሞ ዝም ብላ
አየሩ ላይ እፍጥጣ ከቀየች በሁዋላ ድንገት ትጮሃለች።

"ብር ያለው ደደብ ... ደደብ ሁላ ... ብር ብቻ ... ደደብ የያዘው ብር የደ
ነው" ትልና እጇን ከፖሊሶቹ ለማስለቀቅ ጮትታ ጮትታ ቢያቅታት "እ እ ...
አረታዋን ታስነካዋለች። ይዘዋት ከመጡት ፖሊሶች አንደኛው ትከት ባለው ድ

"ኧረ ጮበዝ እስኪ አንድ በሉን፣ ካቅማችን በላይ ሆነሰች" አሰና ትንሹ
ላይ ልትንሰው ስትሞክር የተወችውን በምራት የራሰ የእና ምልክት አሰና ትንሹ
ከሕልምሮዋ መታወክ የተነሣ ሊያጋገራት እንደማይችል የተገነዘበው አሰና
ድምፁን ከፍ አድርጎ፣

"ሲስተር መመርመሪያ አልጋ ያለበት ክፍል ብናስገባት? መድኃኒት ከተሰጣ
በጓላ መተኛቷ አይቀርም። በዚህ ሁኔታዋ ምንም ልናናግራት የምንችል አይመስለኝም፣
የዶክተር ምስክር ቢሮ ክፍት ነው እንዴ?" አለ፣ አውንም ዓይናቸውን ከሕሙምቷ ላይ
ላይንቅል።

"እውነትህን ነው ልጄ፣ ትንሽ ሰፋ ሰሰሚልም እባ ይሻላል መሰል። ታዲያ
አሰብክ? ኢንጂክሽን ላዘጋጅ እንዴ?" አለች፣ ፖሊሶቹን ወደ ቢሮው አየመራች
በራን ለመክፈት ከቁልፎቿ መሃል ለመምረጥ እየሞከረች።

"ጥሩ ... እኔ እሰኩማያት ለምን 100 ሚሊግራም ሳርጋክቲል አታዘጋጂላትም
አለ፣ አልጀሪ ብላ መሰሉ ላይ የምትንፏቀቀውን ሕመምተኛ ወደ ክናሱ ለማዘንፈል
የሚሳትቷትን ፖሊሶች ለማገዝ እየሞከረ። ሴሎች ሁለት የጽጻት ሠራተኞች
ተጨምረው ከግራና ከቀኝ ይዘዋት ክፍሉ ውስጥ ካለው አንዱ መቀመጫ ላይ
ሊያስቀምጧት ሞከሩ። እንዲት ብሎ የምርመራ ጥያቄውን እንደሚጀምር እንጂ
ከሕመምተኛዋ ፊት ለፊት ካለው የጠረጴዛ ጠርዝ ላይ ደግፍ ብሎ እንደ መቀመጥ አለ፣
የተቦጫጨረ ፊቷ ግርማቱና እድፉ ተደራርበበት በደሀና ቀን የፊቷ ቀለም ምን ይመስል
እንደ ነበር ለመገመት አዳጋች አድርገታል።

እግሮቿን አመናጭራ ስትቀመጥ እርቃኗ በከፊል ተገለጠ። አጠገቧ ከቀሙት
የጽጻት ሠራተኞች አንዱ ቀሚሏን ልታለብሳት ስትሞክር ዓይኖቿን እያጉረጠረጠ
ስትጮህባት ደንገጣ እጇን እሳት እንደ ነካ ሀጻን ሰበሰበች። ወደ ሴላው ትከ ዙ
ስታየው ቀየችና ድንገት "ብር ያለው ደደብ" ብላ ስትጮህበት እሱም ከው አለ፣ ቀኝ
እግሯን አወናጭፋ ልትረግጠው ስትል በፍጥነት ዞር ብሎ ለትንሽ ሳተችው። ሚጣ
ከንባባቸው የቀየ እግሮቿ እስከ ቁርጭምጭሚቷ በላይ ድረስ አቧራ ጠገበሞሉ።
በእንቅፋት የተወለጋገዱት የእግር ጣቶቿ ዋፍሮች ያለ ቅዋ አድገው የጹር እግር
መሰለዋል። እዛና እዚህ የተቦጫጨቀው ቀሚሷ እድፍ ጠገቦ የፋብሪካ ቀለሙን
ለመገመት እንኳ አይቻልም።

ድንገት ብድግ ብላ ወደ በሩ ለመሮጥ ስትንደረደር ጥቂት ጸጥ ብሎ የነበረው ክናሱ
እንደገና ተረበሸ። እሷን ወደ ቦታዋ ለመመለስ በተፈጠረው ርብርብና ትግል የረፋዱ
ፀሐይ ያሞቃት ቢሮ የባሰ ታመቀች። በግብግቡ ሳቢያ ከየሰዉ ሰውንትና ሚማ እየተነ
የወጣው ጠንካራ ጠረን ሴላውውን እዋወለመለው። ሲስተር ዘቢባ ያዘጋጀችውን

መርፌ ብንድ እጇ ይዛ በሩን ከፍታ ስትገባ የታመቀው ክናሱ ሽታ ንፍትር ሊጥሳት
ከደረ ፊቷን ሞምድድ አደርጋ፣

"ውይ ውይ ምነው? እንዴት ታፍናኋል ክናሱ ልጂ ... ኧረ መሰኩቱን ከፈጂው
እስኪ ይብ" አለች፣ በመስኮቱ በኩል ያለችውን የጽጻት ሠራተኛ። የተዘጋጀውን መርፌ
በሲስተር ዘቢባ እጅ ስታያ በጨዋ ኬትና በመወራጨት ለያሸ ለከልካይ አስቸጋሪች። እንደ
ምንም ተሳብረው ይዘዋት ረጋ ስትልላቸው ከቀኝ ታፋዋ ላይ ተመጋች። እንደ
አሮር ደቂቃ እየተወራጨች፣ የሆነ ያልሆነውን መቀባጠሯን ቀጠለች። ከዋቂት ደቂቃ
በኋላ መድኒቱ መሥራት ሲጀምር፣ ትንሽ ቅዝዝ ብላ ቀይታ እንደ ማንቀላፋት ስትል
ተንገዳው የመመርመሪያ አልጋው ላይ በትክክል አስተኟት። የጽጻት ሠራተኞቹ ደንግ
ብገቱ ወንበር ላይ ቁጭ ቁጭ ብለው በረጅሙ ተነፈሱ። የጽጻት ሠራተኞቹ ደንግ
የሆነ ነገር እያያቸው፣

አንዲ ሴላውውን እያያች፣

"ዶክተር፣ ካርዷ እስኪመጣልህ ከፖሊሶቹም ቢሆን የቻልከውን ያህል ሂስትሪ
ውሰዳ። አልጋ ከተገኘ አማኑኤል ማስተኛት ሳይኖርብን ይቀራል ብለህ ነው? እንዲህ
ሆና መቼም ወደ እስር ቤት ወይ እንደገና ወደ ጉዳና መመለስ የምትችል አይመስልኝም።
ተመልሳ ባትንቃብን ቶሎ ብለን የሚደረገውን ማድረግ አለብን" ብላ፣ ለመውጣት በሩ
ላይ ከደረሰች በኋላ መለስ ብላ፣ "ውይ የኔ ነገር ረስቼው፣ የሚመብቁህ ሰዎች አሉና፣
ለሰሞ ልቅጠራቸው ወይስ? ክትትል ናቸው መሰለኝ፣ የምሳ ሰዓትህም እጂው መቃወስ
ነው አስ" ስትል፣ ሰዓቱን እየት እያደረገና፣

"ኧረ ግድየለም፣ አለኝ ትንሽ ሰዓት፣ አስካውን ጠብቀው ኝማ አያቸዋለው።
ብቻ ትንሽ ይታገሱኝ፣ ንገሪያቸው" አላት። ሰሽ ብላ ወደም ታንኮራፋዋ ሕመምተኛ
አየ።

"ኧ...ረ እነሱማ በደስታ ይጠብቁሃል። ያው የሚሆነውን እያዩ አይደል? ውይ
ለምድሊላሂ ... እ...ን...ዲ ሰላም ወረደ እኮ። እንዲያው ላርጋክቲልን የፈጠረ
እጅ! በእውነት አላህ ዘርማንዘሩን ይባርክ" አለች። መድሃኒቱ ባይኖር ምን ሊሆን
እንደሚችል በማሰብ፣ ተንፈስ ብላ ከክፍሉ ውጣች።

በሚቀጥሉት አሥር ደቂቃዎች ፖሊሶቹ የሚያውቁትን ሁሉ ነገሩት። ካርዱ
ላይ ማስታወሻውን ሜር ሜር አደረገና ሕመሟ 'ስኪዞፍሬኒያ' መሆኑን አስፍር
ሙተና እንዳለባት ውሳኔውን ጻፈ። ወደ አማኑኤል የምትተላለፍባትን መሸኛ ቅጽ
ሞልቶ ካርዷ ውስጥ አስቀመጠ። ፖሊሶቹ እንደ ነገሩት ከሆነ ኦሊምፒያ አካባቢ
ሁሉም የማትጠፋ 'እብድ' ስትሆን ሰሞኑን ግን ሕመሟ ብሶባት ነበር የከረመችው።

ከለንድ ቀን በፊት ወደ ሦስት የሚጠጉ የቀሙ መኪናች መስተዋት ሰባብራ ነው
ፖሊስ ጣቢያ ወስደው ያሳደሯት። አስር ቤቱ ውስጥ ከቱጥጥር ውጪ ሆና የሚያደርጉት
ሊጠፋባቸው እንዳጣ ነገሩት። ያካባቢው ሰዎች ዝናሽ ብለው እንደሚጠሯት
ብቻ እንጂ ስለ እርሷም ሆነ ስለ ቤተሰቧ ሴላ ምንም እንደማያውቁ አስረዱት። ተኝታ

መታከም እንዳለባት ነገሯቸው ወደ አማኑኤል የሚወስዳት ትራንስፖርት እስኪመጣ እነርሱ እየጠበቋት ሊቆዩ ተስማሙ ።

ዝናሽን ከፖሊሶቹ ጋር ትቶ ወደ ራሱ ቢሮ ሄደና የቀሩትን ሕመምተኞች ማየት ቀጠለ ። የመጨረሻ ሕመምተኛውን አሰናብቶ ሲቀመጥ ፣ ባለቤቱ ንጹሕ ፎጣ መደወሏን ተመለከተ ። አነቷ ጋ የነበራቸው የምሳ ቀጠሮ ገና አሁን ትዝ አለው ። አዋር የገኪም ማስታወሻውን ካርዱ ላይ እየጻፈ ሲደውልላት ወዲያው አነሳችው ። ስለዛም ነው? ምሳ በዛ እንዴ? አለች ፣ ረጋ ባለ ለስላሳ ድምፅዋ ።

"ገባም ነው ፍቅር ፣ ያው ታውቂው የለ ። የሚገርምሽ ምሳውን እሳቃለሁ ረስቼው ነበር ። አንድ በጣም የተረበሸች ሕመምተኛ ባለቀ ሰዓት ፖሊሶች አምጥተው እሷ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ወሰደብኝ ። አሁን ግን አልሞስት ጨርሻለሁ ፣ ትንሽነው የቀረኝ ብዙም አልቆይ እመጣለሁ" አለ ፣ እስክርቢቶውን በጣቶቹ መሃል እያሽከረከረ ።

"ታዲያ የምትደርስ ይመስልሃል? አንቱ ደጋግሞ እየደወለ ነው ። ትውቃለህ እኮ እሱን ። ብዙ ሰው ሳይጠራ አይቀርም ። ትንሹ ልጄም ዛሬ ማታ ወደ ሰገነት ትመለሳለች መሰለኝ" ስትል ፣ ከወንበሩ ተነሥቶ ወደ መስኮቱ እየሄደ

"እስኪ ቆይ ፣ ሲስተርን እንዴ ላናግራት ። ያልኩሽን ሕመምተኛ ወደ አማኑኤል ለመላክ እየሞከርን ነው ። ግን እኔ ገና ቤት መጥቼ እንደገና ሰሚን ማዘጋጀት ተይደብ ስንደር የባሰ እንዳናረፍድ ። ለምን እናንተ ቀድማችሁኝ አትሄዱም? እኔ ከዚህ በቀጥታ መምጣት እችላለሁ" አለ ፣ የተሻለ ሐሳብ ስለ መሰለው ።

"ጥሩ አይቀርም ፣ እንደርሱ እናደርጋለን ። አንተ ግን ሳትጠፋፍ በቶሎ ለእሑድ ድረስ ። ለእነርሱ እኔ እነግራቸዋለሁ"

"ግን መኪናስ ... ምን ታደርጋላችሁ ታድያ? አታቲም ሰምሳው ትመጣለች እንዴ? እሷ ልታደርሳችሁ ከቻለች ብዬ ነበር" አለ ፣ በመስኮት ውጪ ውጪውን እያየ ። እናቱን ወይዘሮ እታለምን ከልጅነቱ ጀምሮ አታቲ ነው የሚላቸው ።

"እንዴ ምን ማለትህ ነው? አንቱ እንዳትቀር ደጋግሞ ነው የነገራት ። እሷም ተዘጋጅታ እየጠበቀችህ ነበር እኮ ። በቃ አልያዝህ የኔ ፍቅር ። ታድያ ... ረፈደ ብለህ በዛው እንዳትቀር ደግሞ ፣ እሺ?" ብላ ስታስጠነቅቀው ፣

"እ-ይ-ደ-ረ-ገ-ም ... በቻልኩት ፍጥነት እመጣለሁ" አለ ሳቅ ብሎ ። ስልኩን ዘግቶ ትንሽ ተረጋጋቶ በጸጥታ ደጅ ደጁን እያየ ማሰብ ጀመረ ። ወዲያው 'ብር ያለው ደደብ' የሚለው የዝናሽ ስድብ ቀመስ ቃሏ ትዝ ሲለው ፈገግ አለ ።

'ብር ያለው ደደብ! ህም ... ድንቅ ስድብ ነው ። ደደብ ከሆኑ ፣ ብር የሌለውስ ቢኮን ምን ለውጥ አለው?' አለ ለራሱ ድምፁን አሰምቶ ። እንደዚህ ዓይነት ስድብ ሰምቶም ስለማያውቅ ገርሞ ብሎታል ። ምናልባትም የተያያዘ ታሪክ ሊኖራት እንደሚችል ገመተ ። ቢሮውን ዘጋግቶ ሲስተር ዘቢባ ወዳለችበት ቢሮ ሲደርስ ስልክ እየደዋወለች ነበር ። ከፊት ለፊቷ ካሉ ወንበሮች አንዱ ላይ ተቀመጠ ። የያዘችውን ስልክ ዘግታ ወደ እርሱ ቀና አለችና ፣

"ያስተናገዱ ጉድ ነው ስ ፣ አማኑኤል ሊቀበሏት ተስማምተዋል ። ችግሩ አምቡላንስ ማግኘት አልቻልኩም ። ፖሊሶቹ ደግሞ የነሱን መኪና እንዲወስዷት ለመጠየቅ እንደማይችሉ ነው የነገሩኝ ። እዚሁ ከቀየች ደግሞ አምቡላንስ እስከናገኝ መጠበቅ ግን ማግኘት ነው" አለች ፣ ግራ ግብት ብሏት ጠረጴዛውን በያዘችው እስክርቢቶ እየቆረቆረች ። ቢሮው የጠዋቱ ግርግር ቀለል ብሎት ባዶ ሆኗል ። አቧራ በለበሰው ወለል ላይ የወዳደቁ ወረቀቶችንና የሚጣሉ ኩባያዎች እያየ ቀየና ቀና ብሎ ፣

"በለፈው እንደዚሁ አምቡላንስ ማግኘት አቅቷቸው በራሱ መኪና አንድ ሕመምተኛ አማኑኤል አድርሶ እንደ ነበር ዶክተር ምስክር ነግሮኝ ነበር ። አማራጭ ከሌለ አንድ ቀጠሮ ስላለኝ እግረ መንገዴን አድርሻያት በዛው ልሄዳ ታድያ" አለ ፣ ውጭ ቢሰጧት ... ... ላይ ትቶ መሄዱ እየከበደው ።

"ጎረ ምን በወጣህ ዶክተርዬ ፣ ይሆን ያሀል ያቀየሁህ መች አነስ ። በል ተነስ ፣ ደግ ልጅ ። ቀጠሮህ ይረፍድብሃል ። እኛው እንዳመጣብን የሆነ መፍትሔ ፈልገን እንልካታለን" አለች ። ሐሳቡን ባትጠላውም ከዛ በላይ እርሱን ማስቸገሩ ከበዳት ።

"ግዴለሽም ሲስተር ፣ ሁሉም ነገር ዝግጁ ከሆነ ምንም አይደለም ። እኔ መኪናዬን ተረብላደርጋትናእንዳፍታ በዛው ጥያትላልፍእችላለሁ ። ብቻ እንዳታስቸግረን ጸሎት አድርሽልን ።" ብሎ መግደርደሩ እንደማያዋጣ በመረዳት እያቅማማች ተስማማች ። የሳ ገብቶ ቀጠሮው ምን ያህል እንደ ረፈደ እያወቀ ህመምተኛ አማኑኤል ካላደረሰኩ ብሎ የመግደርደሩ ምክንያት አልገባውም ። ትከሻውን በውስጡ ሰበቅ አድርጎ ነገሩን ለመርሳት ሞከረ ። በራቱ ላይ ትንሽ ቆም አለና "እምም ... ለማንኛውም መንገድ ላይ እንዳታስቸግረን 10 ሚሊግራም ቫልዬም ብትጨምሪላት ጥሩ ነው መሰለኝ ሲስተርዬ" ብሎ መኪናውን ለማቅረብ ወጣ ።

በርግጥም የመድኃኒቱ ጉልበት እየደከመ ስለ መጣ ዝናሽ በከፊል ንቅት መለፍለፍ ጀምራለች ። ተጨማሪ መርፌውን ከሰጧት በኋላ ተጋግዘው መኪና ውስጥ አስገቧት ። የኋላው ወንበር ላይ እሷን ከመሃል አድርገው ፖሊሶቹ ግራና ቀኝ ተቀመጡና ወደ አማኑኤል ተንቀሳቀሱ ። ውስጥ ለውስጥ ያለውን መንገድ በትክክል ስለማያውቀው ፣ የሚንዳት ቶሎ ታርቆቱ ቢጨምርበትም በቀለበት መንገዱ መሄዱን ነው የመረጠው ። የሚንዳት ቶሎ ታርቆቱ ... ጥሩ ጉልበት ስላላት ባዶው የቀለበት መንገድ ብዙም ጊዜ ሰርፍ አርጊ ብትሆንም ፣ ጥሩ ጉልበት ሰላላት ባዶው የቀለበት መንገድ ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም ። ከፖሊሶቹ ጋር ጥቂት ቃላትን ከመለዋወጥ በቀር ባብዛኛው በጸጥታ ነበር የሄዱት ። ወደ ጦር ኃይሎች አካባቢ ሲደርሱ በከፊል የነቃችው ዝናሽ የቂት መወራጨት ጀመረች ።

"እኔ እዛች ቤት አልሄድም" እያለችና የማይገባቸውን ሌሎች ነገሮች እየዘበራረቀች መጮህ ጀመረች ። የጦር ኃይሎች አደባባይን ዞረው ተመልሰው ወደ አማኑኤል አቅጣጫ ሲያቀኑ ደግሞ ትንሽ የተረጋጋች መሰለች ።

'ጦር ኃይሎች አካባቢ ምን ዓይነት ነገር አጋጥሟት ይሆን? ደግሞስ የት ቤት ይሆን?' ብሎ አሰበ ።

በኖኑ መንገድ ወዋታው የውስጥ ለውስጥ መንገዱን አገባደው ወደ ህንጻው አካባቢ የሚወስደው ቀጭን አስፋልት ሙስጥ ገቡ። ወደ አማኑኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ አየቀረቡ ሲመጡ፣ እንደገና እረታዋንና ያዙኘ ልቅቁኝ ብለ መፈራገጥ ጀመረች። የሆስፒታሉ በር ጋ ሲደርሱ ሞራሽ የፊት መንበሩን ብላ መቀመጫውን ለቦቦ ለማዝ አስቦንረች። ሕመምተኖ እንደ ያዙ ያዩት ጥበቃዎች በእጓር አየረዱ ከፍተው የድንገተኖ ክፍሉን ጠቆሙዋቸው። በሳምንት አንድ ቀን ሰንግሻ ቀን ሳይሰጣ ሲሰሚሳ ሲላሞውን ብዙዎቹ የሆስፒታሉ ጥበቃዎች እያው-ቁቸው።

የድንገተኖ ክፍሉ አካባቢ ሲደርሱ አንደ ምንም ተጋግዘው ከመኪናው አውጥተዉ ወደ ውስጥ ይዘዋት ገቡ። የክፍሉ የቀን ተረኖ ነርስ፣ አቶ ሐዲስ ሳያውቁ ሠልጣኝ ነርሶች ጉር በረንዳው ላይ ተቀምጠው ሲያወሩ ነበር የደረሱት። አቶ ሐዲስ እንደ ሻርሻር ሲያዩ ተረባርበው አዝሏቸው። አቶ ሐዲስ ዝናሽን ገና እንዳየዋት አወቋት፣ ጭንቅላታቸውን ብሐዘን እየነቀንቁ

"ዋእይ ... ምን የመሰለች ልጅ፣ እንዲያው አሁንማ ከሰውነት ተረ ሁሉ ወጥታ፣ ሟን ያውቃታል" አሉና ነሰታመሰችኝ ብለው ሰሚን ጠሪት፣ ትኮ አፈጠጠ ችባቸውና ከት ብላ መሣቅ ጀመረች። ወዲያው ደግሞ ተንስታ ሰመዉጣ ብድግ ሰትል ተረባርበው ይዘው አስቀመጧት።

"ኡ ኡ ... መጡ ...መጡ ... ሲገሱኝ እኮ ነው ....ኡ ኡ" እያለች ሳነታ እስኪሰንቀት ጮኸች። ወዲያው ደግሞ ፊቷ ተሰዋውጦ አርጩሜ እንዳየ ህጻን ሰዓት ብላ ፊቷን ብእጆቿ ሸፍና በጸጥታ ከግድግዳው ማእዘን ጥግ ላይ ኩርምት ብላ ስትቀመጥ ክፍሉ አረጭ አለ። የመጣቸበትን ሁኔታ አሰረድቷቸው ራሱ የጻፈውን የመሸኛ ደብዳቤ እየሰጣቸው፣

"እዚህ ብዙ ጊዜ ትመጣ ነበር እንዴ?" ብሎ ጠየቃቸው።

"እንዴ ዋ... ቤቷ ነበር አማኑኤልማ፣ ባመት ሁለት ሦስቴ እዚህ ሳትጥ ልትቀርም። ከትትሏም እዚሁ ነበር እኮ። እናቷ ከሞቱ ወዲህ ግን ይኸው ሦስት አረት ዓመት መሰለኝ አይቼያትም አላውቅ። እንዴት ያለች ልጅ ነበረች መሰለህ ዶክተር፣ እንግዲህ እኔ እንኩዋ ላውቅ ይኸ ሁለተኛ ወይ ሦስተኛ እርግዝናዋ ነው መሰለኝ፣ ሰውነት ከፉ ባዳ ነው፣ አሁንማ ሴላ ሰው መሰላ ዝናሽ መሆኗንስ ማን ያውቃል፣ አይ ፈጣሪ! እንደኖዋን ጎዳና ላይ ወጥታለች ማለት ነው?" አሉ፣ እጃቸውን ከአጠ የሥሪ ልብሳቸው ኪሶች ውስጥ እንደጨመሩ። ሁለቱም ፖሊሶች ባንደነት የለምንታ መልሳቸውን በጭንቅላታቸው ንቅናቄ ሰጡ። የቀጠሮው ጥድፊያ ውስጣቸ ቢኖጠጠውም ስለ ዝናሽ ለማወቅ ያለው ፍላጎቱን መግታት አልቻለም።

"እና ቤተሰቦቿ ይታወቃሉ ማለቴ ከእናቷ ሴላ የሚታወቅ ዘመድ ይኖራል" አለ፣ ከፊቷ የሚጠብቃት ፈተና እየታየው በሃዘኔታ ወደ እርሷ እያየ። ዝናሽ ጥ ከክፍሉ ውስጥ የሉለች ያህል በማጉተምተምና በሰመመን መሃል ጠፍታ አሁንም ከክፍሉ ጥግ መሬት ላይ ኩርምት ብላ ተቀምጣለች።

"አዎን፣ የደሮ ካርዱም ላይ ሰልክ ቁጥር አይሰፋም። ሽረ እንደውም ማናት ያሮ አማረች፣ እዚሁ ካርድ ክፍል የምትሠራ የሰፈራቸው ሰው አለች። እዚህ ቃች በዘ መሆ እኩ አካባቢ እኩ ነው የሚኖሩት ዘመዶቿ። አባቷም በሕይወት ያሉ መሰለኝ። ለደ ሳመታደል፣ ሰው መሆን አብሳ ነው። ሽረ ኤዲያልኝ" አሉ፣ አቶ ሐዲስ እደፍ ሰደ ሳመታደል፣ ልብላቸውን ቀልፈው አጃቸውን ኪሳቸው ውስጥ እንደከተቱ ቀርጠዋ ሮስ ጉሮ የሥራ ልብሳቸውን ቀልፈው አጃቸው አቅመቢስ ቢያስመስሳቸውም ዞርጠው አያሉ፣ ዶክቃ ሰመንታቸውና ሽበቱ ቀልብ ይገዛል። ዘንበመርቅ ሲባል ሌላው ሁሉ ጉቱ ቁመናቸውና ሰል አኳኋራቸው የሰውን ቀልብ ይገዛል። ፖሊሶቹ መሄድ እንዳሰባቸውና በሌላ ጊዜ ድንገኖ ብሎ መጥረው ሲመጡ አየሉ

"ሐመስ ሐመስ እዚህ ሰለምሠራ መኖጀ አያታለው አሰኪ። ታው-ታታለች አንደሚመሰሉ ተናገረው ሲመጡ አሉ

"ሐመስ ሐመስ ሰለ ይሰኛል" ብሎ አቶ ሐዲስን አመሰግኖ ከክፍሉ ሲወጣ በሩ ያኔጉ ልጅም ባንኖት ደስ ይሰኛል" ብሎ አቶ ሐዲስን አመሰግኖ ከክፍሉ ሲወጣ በሩ ላይ ሲደርስ ቀም ብሎ፣ "ይቅርታ፣ እንደው ካወቁ ብዬ ነው፣ ደጋግማ "ብር ያለው ደደብ" ብላ ስትጣ ስትሳደብ ነበር። አዲስ ነገር ነው ወይስ በፊትም የምትሰው ነገር ነው? አገለው ትርጉም ያለው ነገር ከሆን ብዬ ነው" አለ፣ ወደ አርሳቸው ዞሮ።

"እዩ፣ ሁሉም ሲያማት ወይ ስትናደድ ያው ነው። መጀመሪያ ታማ የመጣችው አረብ አገር ሰሥራ ሄዳ ነበር። ከአሠሪዋ መሰለኝ አርግዛ የመጣችው። እና "ብር ያለው ደደብ" የሚሰው ከዛው የተያያዘ ይመስለኛል። አንዴ ጠይቄያት - "ብር ያለው ደደብ አረብ ነው" እንዳልኝኝ ትዝ ይለኛል። በጣም ከተናደደች ትልቁ ስድቧ "ብር ያለው ደደብ" ነው። ሲያማት ግን ያው ሁሉም ሰው ስርዓ "ብር ያለው ደደብ" ነው" አሉት፣ ደብዛዛ ምስጢራዊ ፈገግታቸውን በወርቅ ጥርሳቸው አስጊጠው።

ነገሩ ድብልቅልቅ ስሜትን እንደ ፈጠረበት በሐሳብ ተውጦ ተሰናብቷቸው ወጣ። መጀመሪያ ጳውሎስ ሲያያት ከንጻና ላይ የቀሙ መኪናች መስተዋት ሰባብራ ፖሊሶ ያመጧት አንድ ክሊኒኩን የረበሸች 'እብድ' ነበረች። አሁን ደግሞ ባለ ብዙ ታሪክና ምስጢር፣ ምናልባትም ውስብስብ ህይወት ያላት ሴላ ሰው መስላ ታየችው። ውስጧም ያልታኖረ ሕይወትና ያልተጀመረ ታሪክ ያለው ያልተወሰደ ሴላ ሰው መኖሩን ለማሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገደደ።

በመርካቶ መሃል አጽርጦ በጊዮርጊስ አሳብሮ ሽቅብ ወዶ ሰሚን ማዘጋጃ ሲሄድ በየመንገዱና በየሱቁ፣ በየመኪናውና በየጥጋጥጉ የሚያያቸው ወንድና ሴት፣ ልጅና አዋቂ፣ የኔ ቢጤና ከበርቴ፣ ተሽካሚና አሽካሚ፣ ንጂና ተነጂዎች ሁሉ ለወትሮ ከሆንት ተለየበት። ሴላ ሰው ... ሴላ ፍጥረት መስለው ታዩት። ከመሃል መርካቶ እስከ አዲስ አበባ ጥግ ከተማይቱን ያጨናንቀው ሰው ሁሉ፣ ው-ጪው በሥጋ ተሰብሮ፣ በው-ስጡ ምስጢራዊ ሪቂት ነፍሱን ሰውሮ የሚንከላወስ ሴላ ሰው ሆኖ ታየው።

"ሰው ሁሉ ሴላ ሰው ነው። ው-ጪው ሴላ ው-ስጡ ሴላ፣ ኑሮው ሴላ ህልሙ ለላ፣ ልቡ ሴላ አፉ ሴላ" አለ ሰራሱ። ሃሳቡ ሲወስድ ሲመልሰው፣ ሲወዘወዝ ሲንጠው፣ ከመቼው እንደ ደረሰም ሳያው-ቀው የባስቤቱ አገት ሰፈር ደርሶ ራሱን አገኘው። ለመኪናው ማቀሚያ እየፈሰገ ወዲያ ወዲህ ሲል ስልኩ ጮኸ። ንጹሕ

ከሰሪዎ ። መድረሱን ነገራት ። ልብሱን አስተካክሎ ኮሎኙን አውጣና የቀኝ እጁ መዳፍ ላይ ነስነስ አድርጎ ካንገቱ ነን ላይ በስሱ ቀባ ቀባ አደርገው ። ከመቢናው ዴድርጎ ትንሽ ዘና የማለት ስሜት ተሰማው ። የጠዋት የሆስፒታል ውሎውንና ዝናብን ከመቋ ለማውጣት እየታገለ ወደ ሰፈው ገቢ ዘለቀ ።

ወደ ቤት ሲገባ 'ብር' ያለው ደደብ' የሚለው የዝናሽ ጨኸት አውንም ጆሮው ላይ አንቃጨለበት ። እዚህ ደግሞ ብሙ ብር ያላቸው ሰምጉ ሳሱን ቤቱን ሞልቶታል ። ስለ ዝር ነገሩ ሳይወድ ትንሽ ፈገግ አደረገው ። በየወንበራቸው የተኮለኮሉትን ሰው ሰለ ብሮች እየሳመና እየጨበጠ ሰላምታ ሲሰዋ ሣቁን በእሳር ዝር የተቀጣጠረው ሰው 'ብር ያለው ደደብ' ብሎ ሰድብ አለ በሆዱ ። ያማኑኤል ሕመሙተኞችን፣ የመርካቶ ንብያተኞችንና የሚሰቱ አንት ቤት ድግስ ታዳሚዎችን በቅጽበት በማንጻጸር እዝር ሁሉም ሰው 'እብድ' ፣ ሁሉም ነገር ስም ያልተሰጠው 'እብደት' መሰለው ።

• 5 •

ሴላሙ ከእንቅልፉ እንደነቃ ሰዓቱን ሲመለከት ከሌሊቱ ለአሥራ አንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ይላል ። ከአጠገቡ የተኛችው ንጹሕ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ራሷን ጥላለች ። ደረቱ ላይ ያደረገችውን እጇን ቀስ አድርጎ አንሣና ከአልጋው ውስጥ ሹልክ ብሎ ወጣ ። የሆነ ነገር አትተምትማ ስትገላበጥ ሰውነቷ በከፊል ስለ ተገለጠ ፣ የአልጋ ልብሱን አልብሷት ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደ ።

ፊቱን በቀዝቃዛ ውሃ ሲታጠብ የበለጠ ነቃ ። ፎጣውን ካልጋው ጠርዝ ላይ ጣል አድርጎ ከመልበሻው ፊት እንደቀመ ለራሱ ፈገግ አለ ። ከወዲያ ወዲህ አማተረና ከወደ ጥግ ካለው ሶፋ ላይ ዘና ብሎ ዋቂት ተቀመጠ ። የመስኮቱን መጋረጃ በከፊል ሰብስቦ ውጭውን ሲያይ ገና እንደ ጨለመ ነው ። ለሚንቅላቱ የቀረበውን ሃሳብ ሲያሰላስል ቀየ ፣ ባለ ሙሉ ቀይ ቀለም የስፖርት ቱታውን ለብሶ ኮሽታም ሳያሰማ በቀስታ በሩን ጀንና ወደ ታች ወረደ ። ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ከፍሪጁ ውስጥ ያለውን የውኃ ጀግ አውጥቶ ሁለት ሙሉ ብርጭቆ አከታትሎ በባዶ ሆዱ ሲያንደቀድቅበት አንጀቱ በቅዝቃዜው ተላመሰ ። የሳሎኑን በር ከፍቶ ሲወጣ ፍጥረተ ዓለም በጥብቅ የእንቅልፍ መዳፍ ውስጥ ወድቆ ጸጥ ረጭ እንዳለ ነው ።

የቀቅ ያህል ንቁ የሆኑት ዘበኖቻቸው ጉሮሯቸውን እየጠራረጉ ከማደሪያ ቤታቸው ያረጀ ጋቢያቸውን ተከናንበው በትራቸውን ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ወጡ ። "ደህና አደርክ ሴላሳለም?" አሉ የመኪናውን በር ሲከፍት ወደ እርሱ እየቀረቡ ። እርሳቸውም ከእናቱ ተከትለው ሴላሳለም ብለው ነው የሚጠሩት ። "ወዴት ነው ሰውድቅቱ ልጄ?" ሲሉት ፣

"ትንሽ ሮጥ ሮጥ ልበል ብዬ ነው ሳይሞቅ በማለዳው ። እንዴት ይቀዘቅዛል ባክዎ ... እፍ...ፍ...ፍ ... ብርዱ እንዴት እያደረገም ነው?" አለ ፣ ከውስጥ የጠጣው ውኃ ቅዝቃዜ ከውጭ ከሚነፍሰው ሰስ ነፋስ ጋር ተባብሮ ሽንቁጥ ሲያደረገው ።

"አዩ...ዩ ምናላት ይቺ? ኧረ ይሄ ደህና ነው ፣ ባለፈው ሰሞን የነበረ ቁር

አይሳል፣ አየንት ይሰብር ነበር። ገን እንዲያው በየሀ በሙድት ... ሰሙን የጎ
ስኖርት የምትሥራ ልጅ" አሉ፣ ማለዳቱ አይሉባቸው።

"አብሮት አደባባይ አካባቢ ነው። በጣም ብዙ ሰው በሌሊት እዛ ይሄዳል። ሞ
እሱ አውን ሽ ሳልደርስ ነው የሚጋጋው" አለ፣ ብርዱን ሽሽት ወደ መኪናው ሙን
እየገባ። ከደርግ መውደቅ በፊት ከሀገር ስለ ሙግም አብሮት አደባባይ የሚሉ
ሰም ነው አቶ ላይ የሚቀለው። የውጭ በሩን ከፍተውለት ወጣ። መንገዱ ባዶ ነ
ነበር ከአርጌው አየር ማረፊያ አካባቢ መስቀል አደባባይ ሰመድረስ አሥር ደቂቃ
አልወሰደበትም። ከተደረደሩ መኪናዎች ተርታ አቁመና የመገሸያ ገመዱን ደ
ወጣ። ቀድመው የደረሱ ሰዎች ከመጓዛ መዲያ እየተጋደሉ በግልና በቡድን የቁ
እንቅስቃሴዎችን ወደሚሰሩበት ደረጃዎች ፈጠን እያለ ወጣ።

ጸሐይ የሎሥራውን አድማስ ቀድዳ ገና ባትውጣም፣ ደስ የሚል የንጋት ነፋ
አካባቢውን አየለቅልቀታል። ውር ውር የሚሉ በተለያዩ የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎ
ለስፍራው የበለጠ ድምቀት ለዋተውታል። የልብሳቸው ንብረ ቀለማትና ይዘልቅቅነ
የስፖርተኞች ድምፅ ከእንቅስቃሴያቸው ትርምስ ጋር ተስባጥር ድብልቅነት
በዋድልያ የተመሐረ ርጋታን ፈጥሮበታል። ከባሻገር የሚሰማው የአስፈላጊ
ቴተክርስቲያን ቅዳሴ ደግሞ ከመኪናዎችና ከሰዎች ከሚወጣው ድምፅ ውሱ ገንኖ ክ
ጆት እያለ ይንቀረቀራል።

ቅዳሜ ማለዳ በ'አብሮት አደባባይ' ለሌላሠው ከስፖርትንቱ በላይ የማይረሳ
የልጅነት ትዝታነቱ ያመዝናል። ኢትዮጵያ መጥቶ አዲስ አበባ ካለ፣ ካቅም በዚ
ችር ካለ ጓሙው በቀር አይቀርም። በልጅነቱ ከአባቱ ጋር በየቅዳሜው ማለዳ እሱ
መኖተው መርዋ ወይም በግሮን ሆቴል መዋኘት ሳምንታዊ ልማዳቸው ነበር። ማለዳ እሱ
ደረጃ ትምህርት ቤት ከገባ በኋላ አባቱ በሰራ ምክንያት ወደ አስመራ ስለ ተዘዋ
ብዙም ላይቀይ ደግሞ እሱ ራሱ ወደ አሜሪካ ስለ ሄደ የቅዳሜ ማለዳ አዘውትሮ
ተቋርጦ ቀረ።

የልጅነት ትዝታ ከልብ የማይጠፋ የስሜት ለዛን ተላብሶ ናፍቆትን የሚያሞር
ምስጢራዊ አቅም አለው። ዛሬም ከብዙ አመታት በኋላ ልቡ እስኪጠፋ በስጪ መጓ
እየርጪ ላይ በገንባሩ ላይ ሲንቀረቀር፣ ንውሁን አየር በጥልቅ ሲሰብ፣ አባቱ አጠገ
ያሉ ያህል ይሰማዋል። በቅጽበቲቱ ላይ የንሠውን የጊዚን አገዛዝ ረስቶ አገሩ
የጓልቦሽ፣ አንዲ የአሁ ንሮሽ፣ የትዝታና የመናር መዛግብቱን እያጣቀሰ ዛሬ ያጌ የሆነ
ያህል የውሰጥ ናፍቆቱን የሚቀሰቀስ ደስታ ይሰማዋል። እዚህ መጥቶ ሲርጥ የአባቱ
አብርጋት ይታደስለታል፣ እንደገና ልጅ የሆነ ይመስለዋል።

ላንድ ጉማሽ ሰዓት ያህል በየመሃሉ የራሱን እንቅስቃሴ እያደረገ፣ አንዲ ረጅ
እንዲ ረጋ እያለ ሲርጥ ቀየ። የማለዳዋ ጸሃይ ጨረሯን በአካባቢው ላይ ስትዘራው
የነጪ ሁሉ መልክ ፈካ ብሎ ታየው። ከዚያም ወደ ታች ወርዶ በዛ ብለው በሁን
ሆነው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ከሚሠሩ ወጣቶች ጋር ተቀላቅሎ የነሱን የድገገሞ
እንቅስቃሴ መሰመር ንብቶ መሥራት ጀመረ።

በድንጋጅ መቀመጫዎቹ ላይ አግራቸውን በማፈራረቅ በማውጣትና በማውረድ
የሚሠሩት እንቅስቃሴ፣ ፈጣንና አደካሚ ነው። "አንድ ..... ሁለት ..... ሦስት"....
አስከ አሥር ..... ከዚያ ደግሞ "አሥር ..... ዘጠኝ ..... ስምንት" ..... እስክ አንድ ..... ዙሩ
ያሉ አያልቅም፣ ሲያልቅም ትንሩሽ አያስቀርም። ስፖርት ለገራው የሌላሠው
ሠውነት በድግም ይልቅ ጠንቃ የሚኩረኩር ደስታ ፈጠረለት። የመጣቶቹ መረገ፣
ሳትና መተራረብ፣ አንዲ ከሌላው ቀድሞ ላለማቀም የሚያሳዩት የአልሀ ሲቃ እሱም
ተንዐየዘት ተቀጣቶሏቸው እንርሱት መሰለ።

ብዙዎቹ በስም ስለሚተራሩ የሚተዋወቁ ጎደኛሞች ሳይሆኑ እንደማይቀሩ
ጠርጥሯል። ከአጠገቡ ያለው ልጅ እግር፣ ደልዳላ ውጣት በየመሃሉ የሆነ ቀልድ ነገር
ባል ሲያደርግ ሁሉም ኳ....ኳ.... ብለው ይሥቃሉ። መጀመሪያ ላይ ብዙም ስላልገባው
ላለመሰየት ብሎ ፈገግ ሲል ቀየና የቀልዱ ይዘት እየገባው ሲመጣ እሱም አብሮ መሣቅ
ጀመረ። ከሌላው ቀድሞ ያቀመ ስለሚሳቅበት ሁሉም ጥርሱን ነክሶ ዙሩን ለመጨረስ
ሰውነታቸውን ሲያፍታቱ አንዳንዱ ንግግራቸው ቢያስቀውም ሳያስደንግጠው
አልቀረም።

"ቀይ ገን በረር፣ አንቺ ሙቺ ነው ሙንቻ የምታበቅዪው፣ ወይ ስፖርቱን
ተይውና ይደሽ ክንፍ አስገጥሚ" አለ፣ ሰውነቱ የገዘፈ ከፈት አካባቢ ያለ
ውጣ ከአጠገቡ ያለውን አጥርና ተጭን ልጅ። ዝሆንና ዋንቸል ይመስላሉ ጉን ለጉን
ሲያናቸው። በተረቡ የተማቀበት ቀጭን ልጅ ከእርሱ የወጣ በማይመስል ጉርናና
ደምጽ

"ለማኮብኮቢያ መሳጣሀን ከፈቀድክልኝ፣ በደስታ" ሲል፣ ሁሉም እንደገና
ሣቀ።

"ችግሩ እኮ፣ በዚች አቅምሽ ብፈቅድልሽስ የኔ ጭንቅላት ላይ እንዲት ብለሽ
ትወጪለሽ" ለእሱም ተማቀለት። ከመሳጣው ላይ የሚንቀረቀረውን ላብ በካናቴራው
ሊጠርግ በጸንር የተሸፈን ቦርሜም ሆዱና ለጥ ያለ ደረቱ በከፈል ታየ።

"ምን ችገር አለ፣ ተንደርድሬ ቦርጭህ ላይ ንጥሬ፣ ትከሻህ ላይ እቀምና፣
በቀየታ ከመጓጣህ ላይ አኩብኩቤ መብረር ንዋ" አለ፣ ወደ ታጓች ቦርጪ እየጠቀመ።
"እንደምታውቀው ይሄ ስፖርት ያጓቀለጠው ጉተራ ቦርጭህ፣ እንኳን እኔን ጉማሬ
ያዘለሳል። ለምን ገን ለኤሮቢክ መስሪያ ወይም ለቦክስ መለማመጃ አታከራየውም
በናትህ" የምር፣ በዛውም እኮ እንደ ካናዳ በረዶ ሊቀልጥልህ ይችላል" ሲል፣ ሁሉም
ከትክት ብለው በረጅሙ ሲሥቁ ንዲቱን መደበቅ አልቻለም። ደም በሩ በገንባሩ ላይ
መታየት ጀመረ።

"በቃ ይሄን ጥሙጋ አፍሽን ዝጊ እሺ፣ ፈት ሲሰጡሽ ኮ፣ ከልጅ አትጫወት
አሉ፣ ተባይ ፈት ..." ብሎ፣ ምራቁን ወደ ቀጫጫው ልጅ አቅጣጫ ተፋ።

